# ኡፍ! እባካችሁ እንተኛበት!
# በወያነ ትግራይ መሪዎች ለተጻፈለት ደብዳቤ አንድ የትግራይ ምሁር የሰጠው መልስ
## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ)



*ከሻዕቢያ ጋር ብንጣላም 'ኤርትራን የሚተናኮል' ክፍል ካለ ህወሓት ዛሬም ቢሆን ከኤርትራ ጎን ቆማ የኤርትራ ጠላቶችን ትወጋለች' ሲል የነገረን ከኢሳያስ አፈወርቂ ጎን በስተግራ በኩል እጁን በአክብሮት ወደ ኋሊት አዙሮ የቆመው ስብሓት ነጋ ነው።*

ወደ ርዕሴ ከመግባቴ በፊት ፤በመጀመሪያ እስካሁን ድረስ ለሳምንታት ያክል ወያኔዎችን የሚወጥሩ በርካታ ሰነዶችን ያላንዳች "ሴንሰር" እና የቃላት "ስረዛ" እንዲታተሙ በመፍቀዱ ለዓይጋ ድረገጽ አመሰግናለሁ። አንባቢዎቼን ላስገነዝብ የምፈልገው፤ ዘሐበሻ (ሳተናው) የተባለ ጸረ ኢትዮጵያ ግምባሮች እንዲጨፍሩበት የሚፈቅድ ድረገጽ ባለፈው ወር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን በሚመለከት አንድ ጽሑፍ ልኬለት "አንተ/እሱ" ብለህ የጻፍከው "እሳቸው/እርስዎ" በሚል ቃል ካልለወጥከው ለሕዝብ አላቀርበውም ሲል ክርክሬ ለሕብ እንዳይነበብ አግዶታል።

እንደዚህ ያሉ ሚዲያዎች በተቃወሚ ስም ቆመው ወያኔን የመናገርና የመጻፍ መብታችን አገደን ሲሉ፤ በነጻ ለመጻፍና ለመናገር የምንሻ ነጻ ዜጎች ግን በገንዘብ የሚደጉሟቸው (ለምሳሌ ሻዕቢያ/ኢሳያስን/ብርሃኑን) እና የፖለቲካ መሪዎቻቸው መንካት ያስኮንናል። አይፈቀድም። አሲምባ የተባለው ድረገጽም "ዋለልኝ መኮንን" እና ኢሕአፓን ተቸህ ብለው ጽሑፌ ለሕዝብ እንዳይነበብ አግደውት፤ እስካሁን ድረስ የፖለቲካ ጸበኞች ነን። ኢትኡ-ሚዲያ ወዘተ...ወዘተ... ሁሉም አንድ ባህሪ አላቸው። ሆኖም ኢትዮ-ፓትርዮትስ እና ወልቃይት.ካም የተባሉ አገር ወዳድ አውነተኛ ሚዲያዎች እስካሁን ድረስ ሃሳቤን በነጻ እንድጽፍ ፈቅደውልኝ እስካሁን ድረስ ከሕዝብ ጋር እነጋገራለሁ። እነሱንም አጅግ አመሰግናለሁ። ሚዲያ ሲያፍንህ፤ ሕዝብ አይማርም። መረጃ የሌለው ሕዝብ ደግሞ፤ የመጣ ገዢ

የሚሰይፈው “የመሰዋእሰት በግ” ነው። በቅርቡ ዓይጋ የጀመረው “ዲመክራቲክ-ጀስተር” (አዲስ መስተንግዶ) ወያኔን “ፋሺስት’ ነው ብየ ብከራከርም ያለ ምንም ሴንሰር ሌሎች እንዲሞጉቱኝ በነፃ እንድጽፍ መፍቀዱ በጣም አመሰግናለሁ። ዘሐበሻ (ሳተናው) እና ኢትዮ-ሚዲያ የመሳሰሉ ከዚህ እንደሚማሩ ተስፋ አለኝ (ግን አይማሩም)። አፋኝ የዜና ማሰራጪያዎች በአፈና ባሕሪ ሲጓዙ ሕዝብ/አንባቢ ካልተቃወማቸው አፋኝ መሪዎችን የማንገስ ችሎታ ያላቸው መሆን ብቻ ሳይሆን ሳይመረጡ እራሳቸው ወደ መድረክ ብቅ ብለው ያልተመረጡ የሃሳብ ነፃነት አፋኝ አምባገነን ንጉሶች ወደ መሆን ይሸጋገራሉ።

ሌላው ደግሞ- ሰሞኑን  ኤርትራን አስመልክቼ በጻፍኩት በርካታ ሰዎች በግል ኢመይል ጽፈውልኛል። በተለይ አንድ በዕድሜ ክልል ወጣት ነኝ ብሎ የጻፈልኝ በስድብ ክምር የታጀበ የአንድ ኤርትራዊ ደብዳቤ ደርሶኛል። ካስገረመኝ ውስጥ ስድቡ ሳይሆን “ትግሬዎች እኛን ኤርትራኖችን ወንድሞቻችን ናችሁ ስትሉን ሁሌ የሚገርመኝ ነገር ነው። ከናንተው ጋር ምንም ዝምድና የለንም። ት/ቤትም ቢሆን ይህንኑ ነው የተማርኩት፡ አባቴም ቢሆን ሁሌም ስለ ትግሬዎች ሲነሳ “ከትግሬዎች ጋር ቋንቋ” እንጂ ምንም የሚያገናኝን ነገረ የለም፤ለምን ወንድማማቾች ነን እንደሚሉን አልገባኝም፤ ከነሱ ጋር የምንዛመደው ነገር የለም፡ ብሎ ስለነገረኝ ፤ እባካችሁ ትግሬዎች <u>ወንድማማቾች ነን</u> እያላችሁ “አታደንቁሩን” ብሎ የጻፈልኝ ሳስታውስ የነቀዙ የኤርትራ ምሁራን እና በክህደት ባሕር ለበርከታ አመታት እየዋኙ ያሉት የወያኔ መሪዎች ለኤርትራ ወጣቶች ሕሊና መበላሸት አስተዋጿቸው ምን ያህል እንደተጓዘ በዚህ ወጣት ሕሊና ማየት ችያለሁ።

<u>አሁን ወደ ርዕሳችን እንግባ።</u>

ጀግና ሰዎች የተናገሩት ወደ ብርሃን ይዘውት የሚመጡ ሌሎች ጀግኖች አሉ። ልሳን ሊታፈን ይችላል፡ ከተቀበረበት ቦርቡረው እንዲደመጥ የሚያደርጉ ሰዎችም ‘በተዘዋዋሪ’ የነዚያ ጀግኖች አካሎች የሚሆኑበት ጌዘ አለ። አስቀድሜ እላይ እንደገለጽኩት ስለ ኤርትራ ሰፋ ያለ ሰነድ አቅርቤ ነበር። ይህ ጽሑፍ የዚያ አካል ነውና በዚህ ልደምድም።

አንድ የትግራይ ምሁር ከወያኔ መሪዎች የተጻፈለትን የአብረኸን ታገል የጥሪ ደብዳቤ የሰጠው አስገራሚና የማይረሳ የጥቅስ መልስ እንፈትሻለን። በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ እራሳቸውን በነፃ አውጪነት በመሰየም ብዙ ዜጎች እንዲያልቁ ካደረጉት እስካሁን ድረስ ለፍርድ ያልቀረቡ የወያኔ መሪዎች (ፋሺስቶች) እና

የኢሕአፓ (ኮሚኒስት) መሪዎች ናቸው። ወያኔዎች በትግራይ ተወላጆች ላይም ይሁን በመላ አገሪቱ ያደረሱት አገራዊ ወንጀል፤ የህይወት የንብረት እና የቤተሰብ መፍረስ ወንጀል እስከአሁኗ ደቂቃ ድረስ ለፍርድ አልቀረቡም። ለምሳሌ በትግራይ ተወላጆች ላይ የተሓህት መሪዎች፤ካድሬዎች ፤የሕዝብ ክፍሎች፤ከርቢቶች፤ሰላዮች፤የሓለዋ ወያኔ ሓላፊዎችና መርማሪዎች "በማን ይጠይቀኛል" ተነሳስተው ያለ ሕጋዊ ፍርድ በሕዝብ ህይወት ውሳኔ በማሳለፍ ድብደባና ግድያ፤አፋና እና የንብረት ነጠቃ ወንጀል የፈጸሙ የ'ተሓህት' ታጋይ አባሎች "ለፍርድ እንዲቀርቡ" በወቅቱ የትግራይ አስተዳዳሪ ለነበረው ለነ ገብሩ አስራት በርከት ያሉ ወደ 500 የሚጠጉ የትግራይ ኗሪዎች ፍትህ እንዲያገኙ ጥያቄ ቢያቀርቡም "በረሃ ላይ የተፈጸመ ወንጀል ካለ ለአብዮቱ ተብሎ የተደረገ ስለሆነ አንጠየቅበትም" ብሎ እንደመለሳቸው "ወያኔዎች በ7ጥይት ደብድበው ሞቷል ብለው ጫካ ላይ ጥለውኝ ሄዱ" በሚል ርዕስ በኢጦብና በኔው መጽሀፍ "የወያኔ ገበና ማህደር" ላይ ድያቆን ገብረህይወት ባደረገው ቃለ መጠይቅ ነግሮናል።

እዚህ ላይ ግልጽ ለማድረግ፡ ጠያቂዎቹ የጠየቁት አጭርና ግልጽ ጥያቄ ነበር። "ደርግ በዜጎች ህይወት ጭፍጨፋ ፈጽሟል ብላችሁ ልዩ ፍርድ ቤት ካቋቋማችሁ፤ እናንተም እውነት ወንጀል አልፈጸምንም ብላችሁ ሌሎችን ወንጀለኞች ቀጪዎችና ፈራጆች ከሆናችሁ፤ እኛም በናንተ ላይ ያለንን ክስ ለማቅረብ ዕድል ስጡን እና የእናንትን ገበና የሚመረምር ልዩ ፍርድ ቤትም አብራችሁ ክፍቱና ንጹሃን ከሆናችሁ እሰየው፤ካልሆነም ቅጣታችሁ እንድታገኙ ፍትህ ስጡን" ነበር ግልጽ የሆነችዋ ጥያቄአቸው። ሆኖም "ምን ያለበት ዝላይ አይወድም" እንደሚባለው ፤ ይኸው እስካሁን ራሳቸው ከሳሾች፤ራሳቸው ምስክሮች፤ ራሳቸው ዳኞች፤ ራሳቸው የታሪክ ጸሓፊዎች ሆነው በሌሎች ላይ ሲተቹ፤ ሲፈርዱና ሲቀጡ 26 አመት ሆናቸው።

ለወያኔ ድብዳቤ የተሰጠ ይህ የአንድ የትግራይ ተወላጅ ምሁር አስገራሚ መልስ ያነበብኩት "ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ" ከሚለው በገበሩ አስራት የተጻፈ ታሪካዊ መጽሐፍ ይዤአችሁ ከመግባቴ በፊት፤ ስለ ገብሩ አስራት መጽሐፍ ይቅርታ ተጨምሮበት መጋለጥ የነበረባቸው ይፋ ያልሆኑ የድርጅቱ ወንጀሎችና ምስጢሮች ያለማካተቱ የተቸሁበትን እንደተጠበቀ ሆኖ በመልካም እይታ በተከታታይ ትችቶች የተቸሁበት ይህ መጽሓፍ፤የዳግማይ ወያነ መሪ የነበረው መለስ ዜናዊና ድርጅቱ በሉዓላዊነታችን ያደረሰው ኪሳራ በርካታ ሰነዶች የያዙ ለጀሮአችን አዳዲስ ምስጢሮችን የያዘ የታሪክ መጽሀፍ ሲሆን፤ ትንናንት ማታ ዓይጋ ድረገጽ ስጎበኝ ካሳ ሃይለማርያም ረዳ ስለ አባቱ ብላታ ሃይለማርያም ረዳ

ህይወት እና እሳቸው የመሩት “የቀዳማይ ወያነ” (እኔ የትግሬ ብሔረተኞች በአማራ ላይ ያላቸው የጥላቻ መነሻ ምንድነው? በሚለው አዲስ መጽሐፌ ውስጥ የተቸሁዋቸው፤ ለወደፊቱም ልጃቸው የጻፈውን አዲስ መጽሐፍ አንብቤ ለመተቸት እየጠበቅኩኝ ነኝ። ካደመጥኩት የራሱ ቃለመጠይቅም ሆነ ተናገሩት ከተባለው ንግግራቸው ካሁን በፊት ለተቸሁዋቸው ጉዳዮች የሚያያዙ እና የሚያስረግጡልኝ ንግግሮቻቸው ስለሆኑ ያንን በጊዜው የምናየው ይሆናል።) ይህ በላ 500 ገጽ የሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፈቃድጅነት የታተመው በትግርኛ የተጻፈ አዲስ መጽሐፍ፤ ለየትምህርት ቤቱ መማርያ እንደሚሆን ተነገሯል። ይህንን አስምልክቶ ያደመጥኩት ነገር ያስገረመኝን ሳልጠቅስ ወደ ርዕሴ አልገባም።

በመጽሐፉ የምረቃው ድግስ አዳራሽ ውስጥ የመድረክ አስተናጋጅ ሆኖ ከነበረው (በዕድሜ ወጣት ይመስለኛል) አክራሪ ትግራዊ ብሔረተኛነቱን የሚያስተጋባው ንግግሩ እንዳለ ሆኖ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የብላታ ሃይለማርያም ልጅ የካሳ ሃይለማርያም ረዳ መጽሐፍ ማሳተሙን በከፍተኛ ጭብጨባ እና የትግራይ ሕዝብ ዩኒቨርሲቲውን እንዲያመሰግን አዳራሹን ከጠየቀ በኋላ፤ እንዲህ ይላል።

<<ይህ አዳረሽ ለታሪክና ለስነ ጽሑፍ ደራሲያን ምን ጊዜም ክፍት ነው>> ይላል።

ይህ ከሃቅ የራቀ “ሽወዳ” ነው። መጀመሪያ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (በወያኔ ካድሬዎችና ሰላዮች መያዙን እዛው ሲያስተምሩ የነበሩት መምህራን በሰጡት ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ችለናል) ምርምርና ጥናት (?) የተያዘው በወያኔ አቀንቃኝ ግለሰቦች (ደ/ር) መሪነት ስለሚካሄድ፤ ወያኔዎችና የወያኔ ትግሬ አባሎች ስለ ድርጅታቸው የሚያቀርቡት ታሪክና የሚፈልጉትን ሰነድ ማግኘትና በቀላሉ ለሕትምት ምቹ እንደሚሆን መገመት ይቻላል (ሰነዶችም የተበላሹም “ፎርጅድ” (የተፈበረኩ) ይሁኑም አይሁኑም ለማወቅ ያስቸግረናል። እንደጠቃሚነታቸው መጠቀም ይቻል ይሆናል)። ለእነ ገብሩ አስራት ግን ዩኒቨርሲቲው ሊፈቅድ አይችልም። ምክንያቱ ግልጽ ነው።

ሆኖም ልጁ የሚናገረው <ይህ አዳራሽ ለታሪክና ለስነ ጽሑፍ ደራሲያን ምን ጊዜም ክፍት ነው> ሲል በገብሩ አስራት “ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ” ስለ ዳግማይ ወያነ ገበና እና የድርጅቱ የህይወት ታሪክ፤ከሌሎች ድርጅቶች የነበረው ግንኙነትና ጦርነቶች የድርጅቱ ቁመና በሚገርም ሁኔታ አስመልክቶ የጻፈው መጽሐፍ < ያ አዳራሽ ለታሪክና ለስነ ጽሑፍ ደራሲያን ምን ጊዜም ክፍት

ነው> የሚለው ቅጥፈት ለአስገደ ገብረስላሴም ሆነ ለገብሩ አስራት ለመሳሰሉት የሚያስተናግድ መድረክ እንዳልሆነ አስምሬ ወደ ርዕሱ እንሂድ።

ገብሩ በግሩም አቀራረብ በጻፈው መጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡

<<ተሓሕት በክልሉ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውን የሕዝብ ድርጅት ሓላፊዎችም ለማደራጀት ሞክሯል። ለምሳሌ ያህል ኢንጂነር ታደሰ በዛብህንና መቶ አለቃ ደስታ ታደሰን (የትግራይ ክ/ሀገር የሕ.ድ ዋና ሓለፊና ከጅብ በላይ የሚፈራ፤ደም የጠማው ደብዳቢና ነብሰ-ገዳይ የነበረውን ነው ገብሩ “ደስታ ታደሰ” ስም ከላይ የጠቀሰው) ለመመልምል ሙከራ አድርጎ ነበር። ኢንጂኔር ታደሰ በተሓሕት የምዕራብ ግምባር የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ የነበረው የመለስ በዛብህ ወንድም መሆኑን ተገንዝበን በህቡእ አባልነት ልንመለምለው በወንድሙ በኩል መልእክት ልከንለት ነበር። በአውሮጳ የድሮ ተማሪዎች ማህበር እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበረው ኢንጂኔር ታደሰም አባላችሁ የምሆነው የድርጅቱ ፕሮግራም ትክክለኛ ከሆነ ብቻ ነው የሚል መልስ ላከ።

ይህን መልስ የሰጠን በግሉ ይሁን ከደርግ ባለሥልጣናት ጋር ተማክሮ ይሁን ባይታወቅም የተሓህትን ፕሮግራም ቅጂና ሰፊ ማብራሪያ ልከንለት እሱም ሰፊ መልስ ጽፎልን ነበር።

በነዚህ ጉዳዮች ዙርያ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንደሆነችና ችግሩ መፈታት ያለበት በኢትዮጵያ አንድነት ማዕቀፍ መሆኑን ሲገልጽ የመገንጠል ሙብት ብሎ ነበር እንደሌለም በአጽንኦት ገልጾልናል። ኢንጂኔር ታደሰ የተሓህትን ፕሮግራም እንደማይቀበል ካሳወቀን በኋላ በደብዳቤው መጨረሻ ላይ **<<ኡፍ! እባካችሁ እንተኛበት!**> የሚል የምጸት ሐረግ ማስፈሩ እጅግ ቢያስቀንም በአንድ በኩል ደግሞ የማይሆን ነገር እያስነሣችሁ እትወትውቱን፤ አትረብሹን፤ በቃችሁ፤ የሚል መልእክት እያስተላለፈ እንደነበር ገብቶን ነበር።>>

በማለት ገብሩ በመጽሐፉ ላይ ያሰፈረውን አንድ የትግራይ ምሁር ለተሓህት መሪዎች የሰጠው በታሪክ የማይረሳ መልስ ተመርኩዤ፤ እኔም ኤርትራ ኤርትራ እያላችሁ ሌት ተቀን የምትወተውቱን የኤርትራ አፈቀላጤዎች እነ ሻለቃ ዳዊቶች፤ካሳ ከበደዎች፤ ግንቦት 7 ቶች፤ ተሓህቶች እንዲሁም ተከታዮቻቸው እኔም እንደ ኢንጂኔር ታደሰ **“ኡፍ! እባካችሁ እንተኛበት!”** በማለት ስለ ኤርትራ የለኝን ትችት ደመደምኩ። በሌላ ርዕስ እንገናኝ

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮ- ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ) getachre@aol.com

ጥያቄ ለኢሕአፓ

# ከአዘጋጁ ማስታወሻ፤-

## ጥያቄ ለኢሕአፓ

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) 4/17/2017
Getachew Reda (Editor Ethiopian Semay)



Getachew Reda Editor Ethiopian Semay

ዛሬ የምንመለከተው ለኢሕአፓ አመራሮች፤ ለድረገጽ ተቋማቶቻቸው እና ለተከታዮች አጭር ጥያቄና አስተያየት ነው። ባለፈው ወር እኔን በእጅጉ በአግራሞት ያስደነገጠኝ እና እጅግ ያስገረመኝ ኢሕአፓ ስለ ኢትዮጵያ፤ ስለ አማራ፤ስለ አጼ ምኒልክ፤ስለ ሶማሌ፤ ስለ ኦጋዴን....ወዘተርፈ ያተተበት የቆየ የድርጅቱ ሰነድ ነው የተባለ **"እስኪ ዶሴው ይውጣ! የማን? የኢሕአፓ"** በሚል **በአቻምየለህ ታም**ሩ የቀረበ ለኢሕአፓ መሪዎችና ተከታዮች እንዲሁም ደጋፊዎች እጅግ ፈታኝ የሆነ ሰነድ በተከታታይ ቀርቧል። ይህ ሰነድ እስካሁን ድረስ ከኢሕአፓ መሪዎችም ሆነ ከተከታዮች መልስ ያላገኘ ነው። እኔ በበኩሌ እንዲህ

ያለ ሰነድ ለሕዝብ ይፋ ሲሆን እውነት ነው፤ ይቅርታ፤ ወይንም ውሸት ነው፤ እንዲህ ነው…፤ ተብሎ መልስ መሰጠት ነበረበት። እስካሁን ድረስ መልስ አላገኘም።

ዋለልኝ መኮንን ተችተሃል ተብየ በኢሕአፓ ጀሌዎች ያልተሰደብኩት ስድብ አልነበረም። አሲምባ በሚባለው የኢሕአፓ ድረገጽም "አሲምባ" ጽሁፎቼ ለሕዝብ እንዳይስተናገዱ እስከማገድ ድረስ የደረሰ ብቻ ሳይሆን ስለ እኔ ካርቱን ለጥፎብኛል። በዚህም ጸብ እንደፈጠርን የሚታወቅ ነው። ዛሬ ከዋለልኝ በባሰ "ኢትዮጵያን ፤አማራን፤ ታሪኩን፤አንድነቷን፤ሚኒሊክን.... የሚዘልፍ ሰነድ የኢሕአፓ ነው ተብሎ ይፋ ሲወጣ፤ ኢሕአፓዎች "አፋቸው ሲዘጉ" ማስተዋል ለኔ በጣም ከማስገረሙ በላይ አስደንግጦኛል።

አቻምየለህ በ 6 ተከታታይ ምዕራፎች (ሁሉንም ማግኘት ባልችልም አንዳንዱን ተመልክቼቻቸዋለሁ) በወጣው ሰነድ ላይ አንድ ባንድ፤ነጥብ በነጥብ አንዲት መስምር ሳይዘሉ የተጠቀሱት ክሶች ኢሕአፓ መልስ ካልሰጠበት ኢሕአፓ እንደተቀበለው አድርገን እንወስደዋለን (ኢሕአፓ ስንል ሁሉም "ዲ"/አንጃ የሚባለውም ሆነ ዋናው ኢሕአፓም ሆነ የሚመለከታቸው ሁሉ መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል)። መልስ ካልሰጡበት "ዋለልኝ መኮንን አትንኩብን" እያሉ "ማሃይሞች" ሲሉን እና ሲዘልፉን የነበሩት የኢሕአፓ "ሊቃውንቶች" ካሁን ወዲያ "ከኔ ወዲያ ስለ ኢትዮጵያ ለአሳር፤ ዋለልኝን አትተቹ... ወዘተ" የሚለው መስመራቸው "የኢሕአፓ ሊቅነት" ከባድ ፈተና ውስጥ ገብቷል እና መልስ እንዲሰጡበት እንጠብቃለን። ለምን ጠየቅከን ተብየ በድጋሜ እንደማልዘፍ ተስፋ አደርጋለሁ። አሎ! አሎ! ሃሎ! ሃሎ! ይሰማል?

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ) Getachew Reda (Editor Ethiopian Semay)
getachre@aol.com

የኢሕአፓ ዘረኝነትና ዛቸው! ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay)

# የኢሕአፓ ዘረኝነትና ዛቸው!

# ጌታቸው ረዳ

ነብሱ ይማረው በገጣሚ ሃይሉ ገ/ዮሐንስ (ገሞራው) ግጥም ጽሑፌን ልጀምር።

በመንቃት ላይ ባሉ ፍጡራን መካከል
ህይወት የምንለው እንደ ጥሬ እህል
በኑሮ ምጣድ ላይ ቢቆላ ቢማሰል
የበሰለው ያራል ጥሬው እስኪበስል!!
(ገጣሚው ገሞራው)

አሁን ትልቅ አገራዊ ርዕስ በመጻፍ ላይ ስለሆንኩኝ፤ ጊዜ ላለመሻማት ስል ሌላ ቀን በሰፊው እስከመለስበት ጊዜ፤ ሰሞኑ ኢሕአፓዎች በድረገጻቸው በአሲምባ ላይ ስለ እኔ የለጠፉትን 'ዘረኛና አግላይ ካርቱን" አማራና ኦሮሞን በማናከስ ዘርን ከዘር ለማጨራረስ በወንጀል የሚከሰሰው ኤርትራዊው ተስፋዬ ገበረአብ ጋር እኔን በማነጻጸር **"እኚህ ሰው ምን ነካቸው ከአማራ በላይ አማራ! የከለላ ታሪክ ፤ጋጋታ ምን የሚሉት?"** በማለት፤ "ትግሬው ለትግሬ" እንጂ ስለ አማራው አያገባውም፤ ሌላው ስለ አማራ የመጨነቅ፤ የመቆም መብት የለውም!' ከማለታቸው ሌላ፤ እጅግ አስገራሚ ካርቱናቸው ደግሞ **"የከለላ ታሪክ"** በማለት እኔን **ለአማራው ሕብረተስብ እንደ ባዕድ ወገን** አድርገው በመሳል፤ ለሰሚው እጅግ አሳፋሪና ዝቃጭ የሆነ የመንደር ብስለታቸውን ለማንጸባረቅ ሞክረዋል።

በፓልቶክ ስሙ "**ፋኖ**" በመባል ወይንም "**አደባባይ**" በመባል የሚታወቀው እዚህ ሳንሆዜ ከኔ ጋር የሚኖር ምስኪን የኢሕአፓ ካልትም ሳይቀር፤ ***"አማራ፤ አማራ ፤የሚሉ ፡ስለ አማራ፤ ስለ ምረሽ የወገኑ ሰዎች" አማራዎች ሳይሆኑ ከሌላ ጎሳ የተወለዱ የወታደር ልጆች ናቸው"*** ሲል ከኤርትራዊያን በባሰ መልኩ የዘቀጠ "ዘረኛነቱን" ሲያነበንብ የተደመጠውን በአውድዮ ቀድተው ወዳጆቼ የኢሕአፓ 'ጉድ አደምጥ" ብለው የላኩልኝም አደምጬ ሰዎቹ ጭልጥ ብለው ወደ ዘር ቆጠራ መግበታቸው አጅግ አዘንኩላቸው።

ኢሕአፓዎች ስለ አርበኛቸው ስለ ማርክሲስቱ ዋለልኝ መኮንን እና ስለ ድርጅታቸው የተቸሁትን ተገቢውን መልስ ጽፈው መከራከር ሲገባቸው፡ የነቁ፤የበሰሉ መስለውኝ የነበሩት ሰዎች ወደ ዘረኛነትና ወደ አሉባልታ ሲገቡ ማየቴ በፕሮፓጋንዳው ዘርፍ እጅግ የወረዱ፤ **ቢቆሉ፤ቢቆሉ የማይበስሉ** መሆናቸውን ነው የታዘብኩት።

ስለ ኢሕአፓ በሰፊው ለወደፊቱ የምንነጋገርበት ሲሆን፤ ለአሁኑ ግን ለዚህ ዘረኛ እና ዝቃጭ ብስለታቸው አሁንም በድጋሚ ያስታወሰኝ ነገር ቢኖር “ገዴዎን ለቪን” የተባለው እስራላዊው የሰው ልጆች ተሟጋች እና ጋዜጠኛ “ሰለ ፍልስጢኤማዊያን ሰብአዊ መብት በመቆም እስራላዊያንን በመቃወሙ ምክንያት” ከእስራላዊያኑ የተሰጠው ስምና የካርቱን ጥላሸት **“ከፍልስጥኤማዊያን በላይ ፍልስጢኤማዊ”** ሲሉ ካርቱን ለጥፈውበት የነበረውን አስታውሰውኛል። ይህ በኢሕአፓዎች አልተጀመረም፤ ወያኔዎች ብለውኛል፤ ኦነጎች ብለውኛል፤ ዛሬ የአሲምባ ድረገጽና መሰል የኢሕአፓ ካልቶች የሚለፋደፉት ያንኑ ከአቻዎቸው የቀዱትን ዘረኛና ያልበሰለ ጥሬ መልሳቸው፤ በማስረጃ ለጻፍኩት መልስ፤ በመረጃ አስደግፈው መልስ መስጠት ሲያቅታቸው፤ መልስ ይሆናል ብለው ከወንጀለኛውና “አገሬ ኤርትራ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለም” ብሎ ኢትየጵያን ከከዳ ‘ከተስፋዬ ገብረአብ” ጋር ያነጻጸሩኝን ካርቱናቸውን ለማዬት ትዝብታችሁን ለማኖር ክቡራን አንባቢዎቼ ድረገጻቸውን እንድትመለከቱ እጋብዛለሁ።

ከላይ የጠቀስኩት ፓልቶክ ውስጥ ሆኖ የጀገነ የኢሕአፓ ካልት ደግሞ “ድርጅቱ ድሮ ሲያደርገው እንደነበረው የግድያ ሱሱን በኔ ላይ ለመጀመር የቃጣው ይመስላል”፤ ወጣቱን በማደራጀት *“የድሮ ዶሚናንስ ባሕሪያችን መመለስ አለብን”* ይላል። በማርክሳዊያን ዓለም፤ ለዶሚናንት ባሕሪ መጓዝና መመኘት ምን እንደሚያስከትል እና ምን እንዳስከተለ፤ አሁንም ምን እያስከተለ እንዳለ የምናውቀው ይመስለኛል። የዚህ ጉረኛ ሰው የተለፋደደበትን ስድብና የማስጠንቀቂያው ዛቻ ወዳጆቼ እንዳደምጠው ቀድተው በአውድዮ ልከውልኝ፤አድምጬው፤ የካልት ድፍረት ምን ያህል ርቆ አንደሚሄድ አስገርሞኛል። ይህ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ነው።

ኢሕአፓዎች ለማስፈራራት የተነሱበትን ሰው ማንነት አለማወቃቸው ይገርመኛል። ወያኔ ዝቶ፤ዝቶ፤ዝቶ፤ ስሜን አጥፍቶ፤ጎሳየን ሰርዞ፤ ያልሆነለት፤ አሁን ምስኪኑ የኢሕአፓ ካልት “ኢሰፓ” ብሎ ሲወነጅለኝ፤ እንኳን ኢሰፓ ልሆን ፤ ኢሰፓ ሲመሰረት አገሪቱ ባልነበርኩበት እና ትርጉሙ ምን ማለት እንደሆነ እንኳን የማላውቀውን ሰውዬ፤ እኔን “ይሻለዋል” ብሎ ሲያስጠነቅቀኝ፤ ‘ተደራጁ እያለ የሚወተውታቸውን ወጣቶቹን “አስልኮ” ነጭ ሽብር ሊያራምድብኝ ካልሆነ በቀር ምን ሊያመጣ አንደሚችል ገርሞኛል።

እነኚህ አርበኞች ናቸው፤ ተውአቸው እያልኩ ስከላከልላቸው ከስንት ወዳጆቼ እየተቀያየምኩ፤ ስከላከልላቸው የነበርኩኝ ሰውዬ፤ ዛሬ ‘ቢቆሉ፤ ቢቆሉ፤ የማይበስሉ ሆኖው ሳገኛቸው፤ እውነትም ከዛው ከ70ዎቹ ምድጃቸው አሁንም እዛው አመዱ ላይ ተዘፍቀው መውጣት እንዳቃታቸው ለማየት ችያለሁ።አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች” ብሎናል ወዳጄ ገብረመድህን አርአያ ‘ እውነትም እኔን ለመነካታተል አምሮአቸዋልና እሰየው! ምርጫቸው ነውና፤ አከብርላቸዋለሁ፤ ለሁሉም ኳሱም ሜዳውም እንሆ! እንፈታተሽ።ጥርሱ ያለቀበት ውሻ መጮህ እንጂ መናከስ አያውቅም፤ ኢሕአፓ በዘረኛነት ቢጮህም “የእኔ

ከአማራው ሕብረተሰብ መቆም” ሊያስቆሙኝ ከቶውኑ አይችሉም! “እንደ እናታቸው ጡት ያጡት እንደሆን እንጂ ፤ “እኔ አማራም፤ ትግሬም አገውም፤ኦሮሞም፤ወላይታም፤ ሐረሪም ሶማሌም.....ወዘተ ወዘተ.... ነኝ” ኢሕአፓ “ባዕድ ነህ” ቢለኝም፤ ስለ አማራ የመቆም መብቴ ከተውኑ መንጠቅ አይቻለውም። እንዴት ደፋር ነው ይህ ኢሕአፓ እባካችሁ? ድፍረቱ ሌላ ሰው ጋር ቢያደርገው እንዴት ባማረበት ነበር። ወይ አለማወቅ!

ኢሕአፓ ‘የዜጎችን ህይወት ሲያደርገው እንደነበረው” መሪና ተመሪ ሳይታወቅ ወደ አናርኪ ተለውጦ ህይወት በጥይት ሲቀስፍ እንደነበረው ሊቀስፍ ይችላል። ተጠያቂነትም አልነበረውም፤ እስካሁን ድረስ ተጠያቂነቱን አልወሰደም፤ “ገደሉኝ እንጂ ገደልኩ አይልም፡ አጥፍቻለሁ ተጠያቂ ነኝ አላለም። ይህ ደግሞ የተጠቂዎች ዝምታ ወደ ስንፍና ተተርጉሟል። እንግዲህ ማሾፍ ከቀጠሉ፤ አንድ የተቀናጀ ጥናት መደረግ አለበት እላለሁ።” የሰው ልጆች ህይወት በማርክሳዊ፤አናረኮዊና ፋሺስታዊ እርምጃው ሰውን የመቅሰፍ መብት በገዛ እጁ ሊኖረው ይችላል። የኔን እና የዜጎችን ጎሳነትና የማንነት መብት’ የመንጠቅ ወይንም የመስጠት” መብት አልተሰጠውም። ሊኖሮውም አይችልም።

ቢፈልግ ፓልቶክ ላይ እንደ እኩያዎቹ ዘረኛ ምላሱን ሊዘረጋ ሊሰበስብ ይችላል። ያንን ዘረኛ መብቱን አከብርለታለሁ፤ ስለ አማራ ማሕበረሰብ መብት መከራከር መብቴን ግን ሊነጥቀኝ አይቻለውም። ወያኔም፤አነግም፤ሻዕቢያም ሞክረውታል፤ ኢሕአፓም፤ ሊላላጥ ካልሆነ በቀር ከቶ አይቻለውም!

አላርፍ ካላሉ፤ “ኢሕአፓ በታጋዮቹ አንደበት” በሚል የማወጣው ሰነድ ይኖራል።ተከታተሉ፡ ይቀጥላል።

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ አዘጋጅ) (Editor Ethiopian
Semay) getachre@aol.com



Ethio Semay


MONDAY, OCTOBER 12, 2015


ማርክሳዊ ርዕዮት አልለቅ ያላቸው የአሲምባ ፈላስፋዎች! መልስ ለአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)

# ማርክሳዊ ርዕዮት አልለቅ ያላቸው የአሲምባ ፈላስፋዎች!

## መልስ ለአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች

# ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)




*"ውይይቴ ከመጀመሬ በፊት በቅርቡ ሁለት ታዋቂ አንጋፋ ኢትዮጵያዊያን*

*ማለትም ጋዜጠኛ ሙሉጌታ ሉሌ (የሏላ ሏላ በመጨረሻ ዘመናቸው እዚሁ ውጭ አገር ሆነው ሲያራምዱት የነበረው አቋማቸው ባልስማማም፤ ከዚያ በፊት ላገራቸው ያደረጉት አስተዋጽ ሚዛኑ ከባድ ስለሆነ ሃዘኔን ልገልጽላቸው ተገቢ ነው) የሙሉጌታ ሉሌን ሕልፈት ተከትሎ "የኤርትራ ጉዳይ" ደራሲና ጋዜጠኛ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ሁለቱም በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ነብስ ይማር ለማለት እፈልጋለሁ።"*

አሁን ወደ ኢሕአፓና የ ያኔ ትውልድ ጉዳያችን ይዤአችሁ ልግባ። ለብዙ ጊዜ ኢሕአፓን ስከላከል የነበረበትን ዞር ብዬ ስመለከት አሁን አሁን እራሴ እያስገረመኝ ነው። ማርክሳዊ ጥማታቸው ዛሬም እየተንከባከቡት መሆናቸው ስመለከት ባለማወቄ የሰጠሁዋቸውን ድጋፌ በዚህ ትችት ልሳበው።

ባለፉት ሁለት ሳምንታት "የአዲስ አበባ ቀ.ሃ.ስ.ዩ" የተማሪዎች አንጋፋ መሪ እና "ኢሕአፓ ነበር" ተብሎ በመስራቾቹ የተነገረን ዋለልኝ መኮንን ላይ ባቀረብኩት ትቶልን በሄደው አመለካካቱ ላይ፤

**"በአሁኑ ወቅት የዚያን ትውልድ የትግል ታሪካ የማንቋሸሽና የመከለሱ ዘመቻ ለምን አስፈለገ?"** በሚል ርዕስ ለኔ መልስ ተብሎ በአሲምባ አዘጋጆች በድረገጻቸው የተለጠፈው አንቤዋለሁ። "ያ ትውልድ" ብለው ለሰየሙት ያ ትውልዳቸው የተከተለው ማርክሳዊ/ፋሺስታዊ ርዕዮት፤ ዛሬም አልለቅ ብሎአቸው ስለ ማርክሳዊ ርዕዮታቸው ጥብቅና ቆመው፤ እንደ እነ ዋለልኝ የመሳሰሉት በዘመኑ የነበሩት ማርክሳዊያን ያስተማሩትን መስመር እስከዛሬ ድረስ አፍራሽ ሆኖ ኢትዮጵያን እያተራመሰ ያለው ማርክሳዊ/ሌኒናዊ/ማኦዊና ስታሊናዊ ርዕዮት አትንኩብን፤ከቶውንም ማርክሲዝምን አታንቋሽሹብን ሲሉ መከራከራቸውን አስገርሞኛል።

ያ አልበቃ ብሎ፤ ኤርትራዊቷ ማርታ ለኤርትራ ትግል ስለመቆሟና ዋለልኝም ምናልባት ከእርሷ ጋር ከነበረው ቀረቤታ አንጻር ሲታይ በእርሷ ፍቅር ተነድፎ የኤርትራን ጥያቄ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ሕሊና ተቀባይነት

እንዲኖሮው የመጣሩንና ፤ከዚያም አልፎ ዓለም ድጋፉን እንዲሰጣቸው ለማድረግ ለአይሮፕላን ጠለፋው ያደረገችው ግፊት ከጥቂት አመታት በፊት እንደሚኖር ከአስመራ ከተማ የተላኩልኝ የታተሙ የኤርትራ ፋይሎችና፤ ኢትዮጵያዊያን ታሪክ ጻሐፊዎች ከፍርድ ቤት ያገኙት የማርታ የክስ ማሕደር በማገናዘብ ባቀናበርኩት መሰረት ተነስቼ የገመገምኩትን የግል አስተያየቴን በመቃወም የአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች “በርዕሰ አንቀጻቸው” እኔን “ሊቅ” እያሉ በመሸርደድ ተችተውኛል።

ሊቅ የሚለው ቃል ለኔ የማይገባ መስሏቸዋል። አንዳንድ በሊቃውንትነት ማዕረግ ያሉት ሊያልፉት ያልቻሉ አስቸጋሪ ረዢም የትግል ጉዞ፤ ሁሉም አገሩን ለመግባት ሲያሰፈስፍ፤ አልገባም ብዬ የወላጆቼ ቀብርና ሕመም በቅርብ ተገኝቼ ሳላስታምም እና ሳልቀብር ለአገሬ የቆምኩኝ ታጋይ መሆኔን ያሳለፍኩት ህይወት፤ ማንነነቴንና የአገሬን መከራ ለመጪው ትውልድ ለመግለጽ 5 መጽሐፍቶች (ትግርኛ አማርኛ) በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ የቀረበ ብቸኛ ጥናት፤ (ጥናቴም አንድ ፒ ኤች ዲ አንድ ማሰተርስ ዲግሪ ለምረቃ ስራቸው እንደሚረዳቸው አስፋፍተው እንዲያቀርቡት ፈቃድ ለጠየቁኝ ኢትዮጵያዊያን ያደረስኩ) ሁሉም ስለ ወያኔ ገበና የሚያጋልጡ መጽሕፍቶቼና በሺዎች ቁጥር የሚገመቱ የጋዜጣ፤ የመጽሔትና የድረገጽ ጽሑፎቼ ሲነጻጸር ብቸኛ የትግራይ ሰው ስሆን፤ እኔ እራሴ “ሊቅ” ነኝ ባልልም፤ አሲምባዎች የኔን ጥልቅ አስተዋጽኦ ማንቋሸሻቸው ከኔ ይልቅ እኔን ዶ/ር ጌታቸው ረዳ / አንድ ለናቱ/ ኢትዮጵያዊው ገዴዎን (እስራኤላዊው ጋዜጠኛና ታጋይ ገዴዎን ለቪንን በማነጻጸር) rare bird ፤ አርበኛና አገር ወዳድ ወዘተ...ወዘተ... የሚሉ በርካታ ስሞች መጠራቴን አሲምባዎች አያውቁትም አልልም።

## ጥቅስ እንዲህ ይላል፤

1- “ሰሞኑን የዋለልኝ መኮንንን ታሪክ የማጥቂር ዘመቻው ተጧጡፏል። የአማራ ሕዝብ ጠላትም እየተደረገ እየቀረበ ነው። የማርታ መብራቱም የትግል ታሪክ በኤርትራዊነቷ የነሻቢያ መሣሪያ በመሆን እኒዋለልኝን እንዳነሆለለች ተደርጎ የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴም የዘረኞች መጠቀሚያ ሆኖ እንደነበር የሚሰብኩን ሊቃውንት በየመድረኩ ብቅ ብለዋል። ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና የዚያን ትውልድ ትግል ለመሆኑ የዛሬውን የዘረኝነት መነጽር ተላብሶ ለመመልከት መሞከር ስህተት አይሆንም ወይ? “

## እስኪ አንዴ ባጭሩ ልድገመው!?

“የማርታ መብራቱም የትግል ታሪክ በኤርትራዊነቷ የነሻቢያ መሣሪያ በመሆን እነ ዋለልኝን እንዳነሆለለች ተደርጎ የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴም የዘረኞች መጠቀሚያ ሆኖ እንደነበር የሚሰብኩን ሊቃውንት በየመድረኩ ብቅ ብለዋል።”

**አዎ ያ ትውልድ የዘረኞች ፍልስፍና፤የጸረ ኢትዮጵያ ክፍሎች መፍለቅያ፤ የኤርትርያኖች ትግል መጠቀሚያ ነበር። እንዲያውም ካለችሁ እማ፤** ያ ትውልድ የሚባሉ እነማን ነበሩበት? ኤርትራኖች፤ ወያኔዎች/አነጎች/ኢሕአፓዎች!!!! እነኚህ እራሳቸው ዘረኞች ሆነው የተመለመሉ ጸረ አማራዎች መሆናቸው ከጻፉት የጽሑፍ ስርጭት ማረጋገጥ ይቻላል። አማራውን በነፍጠኛነት ሰይመው በጨቋኝ ብሔር ወንጅለውታል (ኢሕአፓም ሳይቀር!!!!)። ያውም እንነጋገር ካላችሁ እማ፤ አማራን በደመኛ ጠላት የፈረጁት ዘረኞቹ ኤርትራዊያን ‘ማርታ መብራቱን’ መላክ አላስፈለጋቸውም። ምክንያቱም ወይንም በማርታ አማካይኝነት ወይንም በ እነሱ ስብከት ወይንም ….ባንዳች ነገር የተነሳ፤ የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች መሳሪያ የመሆኑ ጉዳይ ዋለልኝ የማርታን ጉትጎታ ያስፈለገውም አይመስልም። እንዲህ ይላል በግልጽ፦

፡

“To applaud the ELF is a sin. If anything favorable is written out, it is automatically refuted by both USUAA and NUEUS. But the Gojjam affair was different. Support for it was practically a show of identity to the so-called revolutionaries.”

On The Question of Nationalities In Ethiopia By Walleligne Mekonnen – Arts IV, HSIU Nov. 17, 1969

**ዋለልኝ በግልጽ የኤርትራ የግንጠላ አቀንቃኝ እና መሳሪያ መሆኑን ነው በግልጽ ከላይ እየነገረን ያለው። ጀብሃን ማሞገስ ማለት በሁለቱም የተማሪዎች ማሕበር ማለትም USUAA እና NUEUS እንደ ሓጢያት ሆኖ ይፈረጃል። ይላል በግልጽ። ሃሎ! ሃሎ! ሃሎ! አሲምባዎች!**

**እንዲህ ይላል፤-**

“…I do not oppose these movements just because they are secessionists. There is nothing wrong with secessionism as such. For that matter secession is much better than nationally oppressive government.፡

“As long as secession is led by the peasants and workers and believes in its internationalist obligation, it is not only to be supported but also militarily assisted.”

**ዋለልኝ ምንድ ነው እያለን ያለው? ከብሔራዊ ጨቋኝ መንግስት ስር ከመኖር አገርን ማፈራረስ ይሻላል። ይላል። የጀብሃን ግንጠላ እንቅስቃሴ ተቃወዋሚ የምሆን ከሆንኩኝ፤ ተገንጣዮች ተገንጣዮች ስለሆኑ ብየ ሳይሆን፤ ግንጣለው የሚመራው ክፍል ሰራተኛውና ገበሬው የእንቅስቃሴው አካል እስካልሆነ ድረስ ነው። በሁለቱም መደቦች ተሳታፊነት የሚመራ ግንጣላ ከሆነ እና ግንጠላው አለማቀፋዊ ላብአደራዊነት ሕግጋት እስከተከተለ ጊዜ ግን ግንጠለው መደግፍ ብቻ ሳይሆን በወታደራዊ እገዛም መታገዝ አለባቸው። ነው እያለን ያለው።**

**ማርታ ከጎኑ ሆና ካላበረታታችው፤ ለዚህም አነሳሽነት ከራሱ ከሆነ ደግሞ እራሱ የገንጣዮች አቀንቃኝ  መሳሪያ የመሆኑ ደግሞ የባሰውኑ “በአገር ግንጠላ አበራታችነት፤ በ የተጠያቂነት ቀለበት መነጽር ክብ ውስጥ ያስገባዋል”። እንዴት ነው ነገሩ!**

ስለ ያ ትውልድ/ ስለ ዋለልኝ አስተምሕሮ ባሁኑ ጊዜ መነጋጋር እጅግ ወቅታዊ መሆኑን የአሲምባ ፈላስፋዎች አልገባቸውም። ብሔር

ብሔረሰብ፤ሕዝቦች እየተባለ በማርክሳዊ ርዕዮት የታጠረ ትምሕርት የተከተለው ዋለልኝ እንዲሁም ኢሕአፓና ወያኔ ያስተማሩት ትምሕርት (አሁም ስራ ላይ ውሎ አሁንም ያስከተለው መዘዝ ገና አልበረደም፤ በቂ ብሔራዊ ውይይትም አልተደረገበትም። አገሪቷም በዚህ እየተናጠች ናት፤ ማርክሳዊ ርዕዮት ካልተገታ ገደብ ካልተደረገለት፤ ገና ትናጣለች። ስለዚህም ትችቱ አስፈላጊና ወቅታዊ ነው።) የአሲምባ ማርክሰዊ ርዕዮት ጠበቃዎች "ዋለልኝ" አትንኩብን የሚሉትም ፡ለማርክሳዊ ርዕዮት ያላቸው ፍቅር፤ ገና እንዳልበረደላቸው ከላይ የጠቀሱትን ፤ ርዕስ ማስረጃ ነው።

ዋለልኝ አማራን አስመልክቶ ስለተቸው፤ መልስ ሰጥቻለሁ። ባለፈው ትችቴ ዋለልኝ መኮንን "ኦርቶዶክስ ሃይማኖትና አማራ" ሁለቱም ላደረሱት የፖለቲካ፤የባሕል፤ የአስተዳዳር ተጠያቂነት ከሚገባው በላይ እያጎላ ወንጅሎአቸዋል። ለዚህም መልስ ሰጥቻለሁ። መላው ኢትዮጵያ ስራ ፈላጊ ሕዝብ የአማራ ስም ካልያዘ ሥራ አንደማይሰጠው ዋሽቷል (ግለሰቦችን እንደምሳሌ እያጣቀሱ ማቅረብ ለሰፊ ውንጀላ በቂ መረጃ ሊሆን አይችልም። የአማራ ስም የያዘ አማራ እራሱ ስራ አልነበረውም። ለዚህም በመረጃ አሳይቻለሁ። ዋለልኝ ስያሰኘው በሁለት ብዕር (በሁሉም ጽሑፎቹ እንሚያደርገው ) እያምታታ የሚጽፈውን ስንመለከት 'አማራው የተበደለ መሆኑንም' አልካደም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ስሜት የሕዝቡ ስሜት ሳይሆን "የነፍጠኞች" (የአማራዎች) ብሔራዊ አገራዊ ስሜት ብቻ እንደሆነ ዋሽቷል። ትግሬዎች የአማራ ስም የያዙት ታሪክ ሃ ብሎ ሲቆጠር "ምኒሊክ፤ሃይሌ፤.........ወዘተ ባልተወለዱበት ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ተያይዞ የመጣ መሆኑን ረስቶ፤ በግድ የአማራ ስም እንሰተሰጣቸው አድርጎ አማራዎችን ይወነጅላል)፤ አማራው የኢትዮጵያን ታሪክና መንግስት ለብቻው እንደመራው ዋሽቷል። ሰለ ባሕል ረጋጭነት፤ ምግብ፤ ሻማ/አለባበስ፤ሙዚቃ፤ ስለ ነፍጠኛነት ሕዝብን በግድ ረግጦ እንዲከተለው ማድረግ፤ አማራውን በማይገባ ወንጅሏል። አማራና የአማራ ስም የያዘ አማርኛ የሚናገረው የጎጃምም ሆነ፤ አማራ የበዛበት የወሎ ሕዝብ በመጥፎ አስተዳዳርና በርሃብ መጠቃቱ የዋለልኝን ማርክሳዊ ውሸት ቁልጭ አድርጎ የሚያረጋግጥ እንደሆነ ገልጫለሁ።

2- *ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና የዚያን ትውልድ ትግል ለመሆኑ የዛሬውን የዘረኝነት መነጽር ተላብሶ ለመመልከት መሞከር ስህተት አይሆንም ወይ?* ብላችሁ ጠይቃችኋል።

እውነት እነዚህ ወንድሞች የሚናገሩትን ያውቃሉ? የዚያ ትውልድ ትግል ምንድን ነበር? የተከተለው ርዕዮት ምን ነበር? እኔው ልመለስስላችሁ!

“ማርክሳዊ ሌሊናዊ” አይዲኦሎጂ/አስተዳዳር ነበር ለኢትዮጵያ ያስተማረውና የተከተለው። በማርክሲዝም ጠባዩ ተነሳስቶ በቡድን ተቧድኖ፤ በጥይት የተደባደበበትም ርዕዮት ይህንን ርዕዮት ለማስፈን ነበር። የዚያ ትውልድ ርዕዮት ማርክሲዝም ማለት “ፋሺዝም” ማለት ነው። ሁለቱም ማርክሲዝም እና ፋሺዝም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። አይደለም የምትሉ የአሲምባ ሊቀውንት በግልጽ እንከራከር።

አዎ እውነት እና ንጋት እያደረ ሲጠራ ነው ብላችኋል። ብዙ ሰዎች ይህንን እውነታ ሊገነዘቡ ሲችሉ፤ ምሳሌውን ብቻ ተገልጾላችኋል። አሳዛኙ ግን እውነታው እንደ ንጋት በርቶ እያለም፤ አሁንም ይህንን ትምህርትና ሃቅ ማገናዘብ አቅቷችሁ “ማርክሲዝም፤ያስተማሩ አስተማሪዎቻችሁና ያስከተሉብን መዘዝ ፤መነጋጋር ፤መተቸት፤መወቀስ፤የለበትም፤ትላላችሁ።” ብዙ ሰዎች የእነ ዋለልኝ ቅስቀሳ “አፍራሽ፤ አናካሽ” መሆኑን ማየት ሲችሉ፤ ለናንተ ብቻ ሊበራላችሁ አልቻለም። ንጋቱ ወለል ብሎ በርቶም ዓይናችሁ አሁንም ማርክሳዊውን ርዕዮት ብቻ አቶኩሮ ተቸክሎ ስላለ “አውነታው ጠጥሮ” ሊታያችሁ አልቻለም። ለዚህ ነው የ ያን ትውልድ ሃዋርያት ያስተማሩት “ትምሕርተ ክርሰቶስ” ነው እና ታቦቱን አትንኩብን የምትሉት።

ያኔ የት ነበራችሁ ዛሬ ወቃሾች የምትሆኑ የሚሉ ሊቃውንቶቻችሁ፤ ለኔ ያስቁኛል። ያኔ ይህንን የ “ኒሂሊስቶች” አፍራሽ የሆነ ባዕዳዊ ርዕዮት ባሕላችን፤ታሪካችን፤አንድነታችን፤ሰላማችን ኩፍኛ ሊያደፈርስብን ነው ብለው ለተከራከሩ ሁሉ፤ ዋለልኝ ምን ብሎ ነው የመለሰላቸው “ፊውዳሎች!” ፤ “ሪአክሺነሪ!”። ያኔ የተቃወሙት እንዲህ ያለ ስም ነበር የተሰጣቸው። ያኔ አንዲያ የተቃወሙትን፤ እንዲያ ያለ ስም ሲለጥፍባቸው ፤ ዛሬ ደግሞ የትምሕርቱን መርዛማነት ስለተቸን እኔን “ሊቃውንት/ሊቅ” እያለችሁ “ማሾፋችሁ” አሁንም ከዋለልኝ አስተምሕሮ ዝንፍ አላላችሁም።

“የያኔ ትውልድ ትግል ለመሆኑ የዘረኝነት መነጽር ተላብሶ ለመመልከት መሞከር ስህተት አይሆንም ወይ?’ ብላችኋል።

ማነው ዘረኝነትን አፍራሽነትን አንባገነንነትን፤ መደባዊ መገዳደልን፤

መደባዊ አምባገነናዊነትንና ግንጠላን፤ ማአከላዊ አምባገነናዊነትን ያስተማረ? ያ ትውልድ!!!!!!!! እንዴት ብላችሁ ጠይቁኝ። መልሱ ፤ያ ትውልድ ያስተማረውና የተከተለው ርዕዮት ፡ማርክሲዝም ነው። ማርክሲዝም ምንን ያስተምራል? በቡድን መቧደንን፤ወገንተኛነትን፤ መደብን፤ገበሬን ፤ወዛደርን/ላብ አደርን ተለያይቶ አንዱ ቡድን አንዱን እንዲያዘው፤ የግል ንብረትና መሬት በላብ አደር ጨቛኝነት በሚመራ በመንግስት ተይዞ/ተወርሶ፤ንብረት አልባ በመሆን፤ማንነቱ ተነጥቆ ግለሰብ/ሲቲዝን የመንግስት ጥገኛ/ጢሰኛ፤ተከራይ/ዲፐንዳንት እንዲሆንና "ኗሪ/ቡድን/ግለሰብ አሜን ብሎ ለላብ አደር ዓለም ዓቀፋዊነት መርሆ እንዲገዛ" ፤ 'አንዱ ቡድን መሪ አንዱ ቡድን ተመሪ ሆነው፤ በስሩ፤ በማአከላዊት ትዕዛዝ እየተመሩ "ሌላወን ክፍል" እንዲጨቁኑት ነበር ያስተማረውና የታገለው። የታገለው ለማን ነበር? ለሥልጣን!? የማን ሥልጣን? "የላብ አደሩ" የበላይነት ሥልጣን! አይደለም እንዴ!?

ለያይቶ አንዴ በጋራ ተቧድኖ አንዱን ክፍል መጨቆን፤ አንዴ ደግሞ 'ላብ አደሩ አምባገነን ሆኖ ሁሉም በስሩ ለይ ሰጥ ብሎ እንዲገዛ መጨቆን፤ አንዴ ደግሞ ገበሬውና ላብ አደሩ ተቧድኖ በሃብታሙና በከተሜው እንዲዘምት ፤ የላብ አደሩ ፓርቲ የበላይነት እንዲኖረው፤ መሪ እንዲሆን ፤ ዜጎች "ተጨቋኞች ሆነው" እንዲገዙ የሚሰብክና የታገለ መርሆ ነበር። ይህ የማርክሲዝም ትምህርት ነው። አሲምባዎች ትንሽ ሳያፍሩ "የአይጥ ምስክሩ ድምቢጡ" እንዲሉ ሆነና ገብሩ አስራትን ለእማኝነት ምስክራቸው ሲያመጡ እንዲህ ይላሉ፡

ከገብሩ በፊት ግን አሲምባዎች እንዲህ ይሉናል፤

"ከሁሉም በላይ ግን በኢትዮጵያዊነት ላይ ከማንም ሰይጣን ጋር አልተደራደረም።" አሲምባዎች ቀልደኞች ናችሁ ጃል!!!!!!

አልተደራደረም? ድርጅታችሁስ ስለ በኢትዮጵያዊነቱ ስለ መደራደሩ ይቅርታ አልጠየቀም? ወይስ ስለምንድነው ይቅርታ ጠየቀ አስተካከለ የሚባለው? ከኤርትራዊያን ጋር ወግኖ ዛላምበሳ ላይ በሃይል ተገድዶ የዘመተን ምስኪን ምሊሺያ ገበሬ ላይ ተኩሳችሁ አልፈጃችሁም? መሪያችሁ ክፍሉ ታደሰ እኮ ነው የነገረን! ወያኔ ምጽዋ ላይ ያደረገው የቅጥረኛነት ተሳትፎ-ታሪክ ኢሕአፓ ዛላምበሳ ላይ አልፈጸመም? የኤርትራን ነፃነት ከመደገፍ አልፋችሁ አልታገላችሁም?

ፕሮግራማችሁ እንዲህ ይላል "ከማወቅ ባሻገር የኤርትራ ሕዝብ ለነፃነት የሚያደርገውን ትግል መደገፍ ነው" ይላል። ከነሱ ጋር ወግናችሁ ነበር ወደ ኢትዮጵያ ሚሊሺያ ምስኪን ገበሬ ያነጣጠራችሁት። ለምን እኔን መጎነታተል መረጣችሁ? ለመወያት ከሆነ፤ ሃቁ ይሄው ነው።

ደግሞ ትንሽ አታፍሩም "የአይጥ ምስክሩ ድምቢጡ" እንዲሉ እንዲህ ትላላችሁ

"ከሁሉም በላይ ግን በኢትዮጵያዊነት ላይ ከማንም ሰይጣን ጋር አልተደራደረም። ለምሳሌ የወያኔ አንዱ መሪ የነበረው ገብሩ አሥራት በቅርቡ በጻፈው መጽሐፍ ገጽ 54 ላይ እንዲህ ይላልለ-" ትላላችሁ፡-

"ኢሕአፓ በፕሮግራሙ ውስጥ የኢርትራ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለበት ከመግለጹም በላይ በዴሞክራሲያ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ከሰላማዊ ድርድር ውጭ ሌላ መፍትሔ ማፈላለግ ዕልቂት እንጂ ሌላ ውጤት እንደማይኖረውም በተደጋጋሚ ይገልጽ ነበር። ይህ የኢሕአፓ አቋም የኤርትራን ድርጅቶች የሚያረካ አልነበረም። የኤርትራ ድርጅቶች ኢሕአፓ በሁለት ጉዳዮች ላይ ጠንካራ አቋም እንዲኖረው ይፈልጉ ነበር። አንደኛው አቋም የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት መሆኑና ቅኝ ገዥዋም ኢትዮጵያ እንደሆነች መቀበል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥያቄው በኤርትራ ነጻነት መፈታት እንዳለበት መቀበል ነበር። እነዚህን ሁለት አቋሞች ከኢሕአፖ ሊያገኙ ባለመቻላቸውም የኤርትራ ድርጅቶች በኢሕአፓ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬና ጥላቻ ነበራቸው…." ወረድ ብሎ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 135 ላይ ለምሳሌ ከኢሕአሠ ተገንጥሎ ወደ ወያኔ የተቀላቀለው ጦር (እነ ታምራት ለይኔ፣ ሕላዊ ዮሴፍ፣ ታደሰ ካሣ፣ ያሬድ ጥበቡ (ጀቤሳ)፣ ኃይሌ ጥላሁን፣ በረከት ስምዖንና አዲሱ ለገሠ ኢሕዴን ብለው በሰየሙት ድርጅት አማካይነት የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ነው ብለው ተቀብለዋል ብሎ ያቀርባል። የአሲምባ ድሕረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል" ይላል ለምስክርነት የመረጣችሁት ገብሩ አስራት፡-

እኛ ትግሬዎች "ሁለት ጉድጓድ የማሰች አይጥ መውጪያዋን አታጣም" እንላለን። ገበሩም እናንተም ሁለት ጉድጓድ በመማስ ለማመምለጫ እንዲመቻችሁ ሁለታችሁ ታሾፋላችሁ። ለምን ነበር የማሻሻ ለውጥ

አድርገናል ያላችሁት? ገብሩ ይህን ማሻሻያ ነው እየዋዠቀ ያለው ወይስ ፕሮግራማችሁ እውን አላነበበም ነበር?

ግንጠላን በማስተማር!፤- ኢሕአፓ/ዋለልኝ "ግንጠላን" የችግር መፍቺያና የመውጪያ ጉድጓድ ምንጭ አድርገው አስተምረዋል። ማርክስዝም የተከተለው ርዕዮት ግንጠላ ለጭቆና እንደ መፍትሔ አድርጎ አስተምሯል። **ወያኔ** የማርክሲዝን ትምህርት ተከትሎ **በ1968** የፋሺዝም/ማርክሲዝን መግለጫ ሲያወጣ፤ **ኢሕአፓ** ደግሞ **በ1976** ከ8 አመት ቆይታ በኋላ ማለት ነው፤ የኢትዮጵያ ሉአላዊነትን በሚጻረር መልኩ ፤ መገንጠልን በፖለቲካ ፕሮግራሙ አካትተ ብቅ አለ። **ወያኔ** **"ጨቋኛ ብሔር"** እያለ (1968) ሲያስተምር **ኢሕአፓ** ደግሞ "ጨቋኙ ብሔር" ሲል ያንን የወያኔ/ትሓህት ፕሮግራም በመደገፍ በ1976 ኣ/ም በፕሮግራሙ ነድፎ አሰራጭቷል። "እንዴ? !!!!!!! በሉ መሪጌታ ሃይሉ" ይላሉ ትግሬዎች። "እንዴ? !!!!!!! አሉ መሪጌታ ሃይሉ"

የአሲምባ ፈላስፋዎች ፕሮግራማችሁ ሳልቀንስ ፤ሳልጨምር እንዳለ እንድታነብቡት ልጥቀስ፤

"የጭቁን ብሔሮችን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት/እስከ መገንጠልና የራሳቸው የሆነ ነፃ መንግስት እስከ ማቋቋም ድረስ መከበር እንዳለበት ማስተማርና መታገል አንዳለብን ሁሉ ጭቁን ብሔሮች በፈቃደኛነትና በእኩልነት **"ከጫቋኝ ብሔር"** ሰፊው ሕዝብ ጋር መዋሃድ እንዳለባቸውም ማስተማርና መታገል አለብን።" ሲል የወያኔን የ1968 ንቱን የፖለቲካ ፕሮግራም ኢሕአፓ በ1976 ከ8 አመት ቆይታ በኋላ ፎቶ ኮፒ **ትክክለኛ ግልባጭ** በፕሮግራሙ አስፍሮታል። ገጽ 23 እና 24 ....ይመልከቱ።

ታዲያ ጌታቸው ረዳ ፤አንድነታችን እንዲጠነክር ተቻችለን ለመኖር ስንል ባሞግሳችሁ እራሴ ላይ ወጥታችሁ ዋለልኝ ለምን ተነካ ብከላችሁ እኔን በማሾፍ 'ሊቅ' እያላችሁ መጎነታታል ምን አመጣው? እንዴ! ትንሽ አታፍሩም? ይህንን ግንጣላ እንዳስተማራችሁ እያወቃችሁ "ያ ትውልድ" ለምን ተነካ፤ ትላለችሁ እንዴ?

አዎ! ያ ትውልድ "ጨቋኝ ብሔር" ሲል አማራ ማለቱ ነው፡ ሌላ ሊሆን

አይችልም። እንዳለ ከዋለልኝ በበሳ መልኩ በፕሮግራሙ ቁልጭ አድርጎ መግለጹ ብቻ ሳይሆን ፤

ኢሕአፓ ኤርትራንም በፕሮግራሙ መርሆ ተደግፎ እንደዚህ ይገልጻታል፡

“የኤርትራ ሕዝብ የራሱን መብት በራሱ የመወስን እስከ መገንጠል ከማወቅ ባሻገር የኤርትራ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለውን መብት **ከማወቅ ባሻገር** የኤርትራ ሕዝብ ለነፃነት የሚያደርገውን **ትግል መደገፍ** ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ የድርጅቱ አቋም ሆኗል። ......የኤርትራ ሕዝብ ነፃነቱን አረጋግጦ የራሱን መንግስት ለመመስረት የነበረው ፍላጎትና ለነፃነት ትግሉ ይሰጥ የነበረው ድጋፍ ከፍተኛ ነበር።...” ይላል።

ሆኖም የኋላ ኋላ፤ አውነትና ንጋት እያደረ ሲጠራለት ኤርትራን ችግር በመገንጠል ሳይሆን “በፌደራል ሩፓብሊክ” መፈታት አለበት ይላል። ፌደራል ሪፓብሊክ ምን ማለት እንደሆነ ባያብራራውም። ይህ ይበል እንጂ የሐገሪቱ ሉዓላዊ የወደብና የመሬት፤ እንዲሁም የሕዝብ ቁርኝት በሚመለከት እርማት አድርጌአለሁ ባለው እርማት ላይ የተጠቀሱት ሉዓላዊ ጉዳዮችን በሚመለከት የመጠየቅ መብታችን በግልጽ አላብራራም።

ታዲያ ያ ትውልድ ጫቋኝ ብሔር በሌለበት “ጨቋኝ ብሔር” ነበር እያለ የወያኔ ትክክለኛ ቅጂ ቀድቶ “የተቀሩት ብሔር ብሔረሰቦች” ብሎ ኢሕአፓ የሚጠራቸው “በጫቋኙ ብሔር” ላይ “ትግል እንዲያካሂዱ” ካልሆነላቸው ደግሞ “እንዲገነጠሉ” የሰበከን ያ ትውልድ በተመለከተው መነጽር መመልከቱ እንዴት ስሕተት ሊሆን ይችላል? ይህ ፍልስፍና ያመጣው ሰበብ አሁንም አገሪቷን እያመሳት ስለሆነ፤ እኔ ይህንን አንስቼ መነጋገሪያ ማድረጊዬ በምንም መልኩ አሲምባዎች ሽርደዳ ውስጥ መግባት አልነበራችሁም።

አዎ ያ ትውልድ ትምህርት ዘረኛነትን ሳይሆን ጭቆናን ፤አምባገነንነትን አስተምሯል። ዘረኝነት በሌላ መለክያው የወያኔን አይነት እስከ መገንጠልን ሰብኳል። አንድ ሎችን ክፍሎች የጨቆነ “ጨቋኝ ብሔር” አለ ብለህ ስታስተምር “ ጨቋኝ በተባለው ብሔር ተወላጅ ላይ ጥላቻ እንዲነሳ መቀስቀስ ነው። ይህ ነው ኢሕአፓ ወያኔ ኦነግ የቀሰቀሱት ትምህርት “ነፍጠኛ/አማራ” (በዋለለልኝ አመርኛ) የሚባል “አንድ ጨቋኝ ብሔር” አለ ብላችኋል። ስለሆነም ጨቋኝ ብሔር ብላችሁ ባስተማራችሁት ቅስቀሳ

ውጤቱ “የአማራን በነፍጠኛነት” ስም መለያ መስጠትና ዛሬ እንዲባረር፤ እንዲጨፈጨፍ ሰበብ ሆኗል። አንድ ዜጋ፤ወይንም ግለሰብ በቡድን እንዲረገጥ ያ ትውልድ እስተምሯል። ለዚህ ነው አሁንም ቡድኖች እነሱን በማይመስል (ላብ አደር፤አርሶ አደር፤ ብሔር፤ብሔረሰብ፤ሕዝብ......) ልዩ ክፍል ካለ ለጥቃት፤ለመረገጥ ምክንያት ሆነ እየተባረረ፤እየተገደለ ንብረቱ፤ ንግዱ እየተቀማ ያለው።

የአሲምባ ፈላስፎች በጽሑፌ ከተስማሙ “ጥሩ” አበቃሁ በዚህ አደመድመዋለሁ ማለት ነው። ካልሆነ ግን በሚቀጥለው ጽሑፌ ማርክሲዝም ማለት ፋሺዝም መሆኑንና ስለ ዋለልኝ በጻፍኩት ላይ ሁለት የኢሕአፓ ምሁራን ከጥቂት አመታት በፊት የጻፉትን ለኔ በዋለልኝ የሰጠሁትን መልስ ተብሎ ባለፈው ወቅት አሲምባ ድረገጽ ላይ የተለጠፈው በዝርዝር አብራራለሁ። ለሁለም ኳሷ ለነሱ ሰጥቻለሁ። እንቀጥል አንቀጥል፤ የናንተ ጉዳይ ነው። እውነት የመጻፍ ነጻነት ትርጉሙ ቢገባችሁ ኖሮ፤ የናንተ እና የመሪዎቻችሁ ጽሑፍ ስትለጥፉ አብሮ የኔንም መልስ እና ትችት በድረገጻችሁ መለጠፍ ነበረባችሁ፤ አለመታደል ሆኖ፤ ያንን ለማድረግ አልፈቀዳችሁም። ወደዳችሁ ጠላችሁ የኔን መልስ ከድረገጻችሁ ለመሸሸግ ብትጥሩም፤ ከቁጥጥራችሁ ውጭ በሆኑ ድረገጾች ከኢትዮጵያዊያን አንባቢዎች (ከወዳጅም ከጠላትም) ዓይን ልተጋርዱት ከቶ አይቻላችሁም። ደግነቱ እንኳን መንግሥት አልሆናችሁ። መንግስት ብትሆኑ የኔን ጽሁፍ እንዲህ ከሕዝብ እይታ የሸሸጋችሁት ፤ በላብ አደር ፓርቲ እየተመራችሁ እመንግስት ሥልጣን ላይ ወጥታችሁ ብትኖሩ ኖሮ፤ በአካል ምን ታደርጉኝ ኖሯል? ትግሬዎች እንዲህ ይላሉ “ንዘረባ አስተውዒልካ፤ ንእኽሊ ኣኾምሲዕካ” ይባላል (ስትናገር አስተውለህ ስትበላም አኝከህ” ይላሉ። አበቃሁ!

አመሰግናለሁ፤

ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay) October 12, 2015

getachre@aol.com

[መስፍን ወልደማርያም-ዋለልኝ መኮንን ሁለት መንትያዎች ጌታቸው ረዳ (Getachew Reda - Editor Ethiopian Semay) Septemeber 28/2015]

## <u>መስፍን ወልደማርያም-ዋለልኝ መኮንን ሁለት መንትያዎች</u>

<u>ጌታቸው ረዳ (Getachew Reda - Editor Ethiopian Semay)</u>

**<u>Septemeber 28/2015</u>**




ወደ ዋናው የመነገገርያ ርዕሴ ከመግባቴ በፊት ባለፈው ሁለት ሰሞን ጉሙዝ ላይ አማራዎች በደረሰባቸው የጎሳ ጥቃት፤ ኢሕአፓን በሚመለከት አስመልክቼ በደመፍላት የጻፍኩት ትችት እንደነበር ይታወሳል። አንዳንድ ሰዎች በኢሕአፓ ላይ በጻፍኩት ትችት፤ በተለይም ስም ጠቅሳችሁ "ሃማ ቱማ (ታጋይ እያሱ አለማዮህን) አስመልከቼ አንደጻፍኩት አድርጋችሁ በመደሰታችሁ የላካችሁልኝ ደብዳቤ እጅግ ከልቤ አዝኛለሁ። ላንዳንዶቻችሁም መልስ ጽፌላችኋለሁ። ይኼውም ፤ ሃማ የኔ አርበኛ እና የግል የትግል ጓዴ ስለሆነ ከቶውንም ሃማን ለማሳዘን፤ በሃማ ቱማ ባትመጡብኝ እጅግ አመሰግናለሁ።

ስንተታች ፖለቲካውን አስመልክተን እንጂ ለጥል ለግል ሽኩቻ አንዳልሆነ እንድታውቁልኝ አሳስባለሁ።ይኼ ደግሞ ሁሌም የምናደርገው ነው። ዩኒክ/ልዩ የሚያደርገንም ይህ ባሕሪያችን ነው። የኔን መነሻ እያደረጋችሁ በየፓልቶኩ ኢሕአፓን ስትዘልፉ አድምጫለሁ። ኢሕአፓን ወይንም እያሱን ቀዳዳ ተገኘ እያላችሁ፤ በየፓልቶኩ የምትዘልፉ ሰዎችም ከዚያ አንድትርቁ አደራ እላለሁ። በተረፈ ኢሕአፓ አለመታደል ሆኖ "ብዙ ባንዳዎች" ትግሉን እየበረዙ አበላሹት አንጂ "ኢሕአፓ" የሚስተካከል ነገር አስተካክሎ፤ የተበተኑትም አባሎቹን አሰባስቦ ባንድነት ትግሉን ቢመበራው፤ ወያኔ ይኼኔ ይገረሰስ አንደነበር በሙሉ ልቦና ነው የምላችሁ። ወደዳችሁትም ጠላችሁትም ፤ ኢያሱ ዓለማዮህ/ሃማ ቱማ አሁንም የትግል ጓዴ እና እጅግ የማከብረው አርበኛ እና ጋዴ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ወዳጆችና ጠላቶች ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። Hama! the Hero, an author, poet, rare icon and the only revolutionary student leader of our time left on this earth. Viva Hama! Head up my brother!

አሁን ወደ ርዕሳችን እንግባ። ሰፋ ያለ ትንታኔ ስለሆነ ጊዜ ወስዳችሁ አንድታነብቡት ይሁን።ለማንበብ የምትደክሙ "አጭር ተጓዠ ደካሞች" ካላችሁ ወደ አጫጫር ዜና አቅራቢዎች ሂዱ። ወዳጆች ሆይ እኛ ጻሐፊዎች ለታሪክ ሰነድ ለማስቀረት የምናደርገው ጥረት ድካም እና የጊዜ መጣበብ የምናደርገው ግብግብ ብትረዱልን እንዴት ደስ ባለን። በዛሬው በዚህ ርዕሠ ጽሑፍ የተመለከቱ በሁለት ታላቅ ኢትዮጵያዊያን ምሁራን ላይ እተቻለሁ።

በቅድሚያ ምሁሩ ፕሮፌሰርና እና እውቅናቸው የገነነው መስፍን ወልደማርያምን እተቻለሁ።ከዚያ ወደ ዋለልኝ አመራለሁ። ከዚያም\\ በሚቀጥለው ሳምንት ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም "ፈጣሪ

የወያኔ ዕድሜ ወንድሞቻችን ሥርዓት ዕድሜው ያርዝምልን" ፡ በማለት፤ የአማራን ዘር ማንዘር በማጥፋት ላይ የሚገኘው ፋሺስቱ የወያኔ የትግሬ መንግሥትን የመረቁበትን እንደበታቸው እተቻለሁ።

ከዚያም ቦታ ካልጠበበ ጋዜጠኛ ነበረች የሚባልላት በእስተ እርጅናዋ በፀረ አማራዎች በዘረኞቹ በእነ ኤፍሬም ማዴቦ የሚመራው "ግንቦት 7 ካድሬና "የኢካዴፍ/ካረንት አፈይርስ አስተባባሪ የሆነቺው ወ/ሮ ብዙ ወንድማገኘሁ/የፓልቶክ ስሟ "ሙያዬ ምስክር" ስለ አማራ መደራጀት ጥላሸት የመቀባትዋ ጉዳይ የተናገረቺውን ከነፎቶግራፍዋ በመለጠፍ እተቻለሁ። ከዚያም ቂጣ ራስ በማለት እራስዋን የምትጠራ "ኦሮሞ ነኝ" ብላ ባንደበቷ የነገረችን፤ ሻዕቢያን እያወደሰች ትግሬውን የምትዘልፍ፤ ለሻዕቢያ ያደሩትና፤ አማራን ሲዘልፉ በቴፕ የተቀዱ፤ በጸረ አማራነታቸው የታወቁት የግንቦት 7 መሪዎችን በመከላከልና በማድነቅ፤ "መርማሪያዋ" ተብላ በብዕር ስም የምትጠራ፤ እጅግ ሲበዛ አውቀቷ፤ለዛዋ እና በመረጃ የተደገፈ ብርቱ የሆነ የመልስ አሰጣጥዋ የሚያረካ፤ ደምጸ መራዋ ኢትዮጵያዊት ታጋይ፤ ይህችን "ትንሽዬ ሕሊና ያላት ቂጣ ራስ" ሴትዬ ምን ብላ ታስተምራት እንደነበር አባ መላ ያወያያቸውን ውይይታቸውን እንመለከታለን። ይህ ለሚቀጥለው ይሆናል። ለዛሬ ግን ይህንኑ ከታች ያለውን እንመለክት።

## ፕሮፌሰር መስፍን፡-

በተለያዩ ምክንያቶች አክብሬአቸዋለሁ። አሁንም አከብራቸዋለሁ። ባለፉት በርካታ አመታት እሳቸውን ለመከላከል ስል ከዘለፉዋቸው ከብዙ ጸሐፊዎችም ጋር ተጋጭቼአለሁ። ለሰሯቸው ብዙ በጎ ነገሮችን አሁንም አክብሮት እየሰጠሁ፤ ግልጽ ያልሆኑልኝ፤

የሚጎረብጡ ስለ አማራ ማሕበረሰብ የሰነዘርዋቸው አንዳንድ አስተሳሰባቸው ግን የአማራው ሕብረተሰብም ሆነ ሌላው ዜጋ እንዲያውቀው ማድረግ እንደ ዜጋ ጠቃሚ መከራከሪያ ሆኖ ስላገኘሁት በዚህ እንወያያለን።

ባለፈው ሁለት ሰሞን በሞረሽ ሊቀመንበር በአቶ ተክሌ የሻው የተጻፈ በኢትዮፓትርዮት እና በወልቃይት.ካም ድረገጾች፤ ኢትዮጵያዊያን ለፕሮፌሰር መስፍን  ጥያቄ እንዲያቀርቡላቸው የዘረዘርዋቸው ጉዳዮች አንብቤ ፕሮፌሰሩ በአንደኛው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ አማራ እና ኦጋዴን ሶማሌዎች የሻከረ ግንኙነት የጻፉት ነገር በሚመለከት አትኩሮቴ ስለሳበው ይህ ትችት በፕሮፌሰሩ ላይ ለማቅረብ ነው።

አንቱ የተባሉ እኚህ ምሁር እና የተከበሩ አዛውንት የሕብረተሰብ አስተማሪ የመሆናቸውን ያህል ስለ አማራ ማሕበረሰብ ያላቸው ግንዛቤ ሙሉውን መረጃ ያጠራቸው ይመስላሉ፤ ወይንም ባልታወቀ ምክንያት የሳሳው ግንዛቤአቸው የተዛጋ ይመስላል።

ብዙ ምሁራን ኤሊቶች/ሊሂቃን እርስ በርስሳቸው በፖለቲካም/ሃይማኖትም ሆነ ባንዳች ምክንያት ሳይግባቡ ሲቀሩ፤ ያንን ቁርሾ/አመለካከት/እምነት ተሸክመው  ብዙውን ቅርያኔአቸው በገበሬው ማሕበረሰብ ጫንቃ ላይ ይጥሉታል። ማሕበረሰቡም ሊሂቃኖቹ በሚያስተምሩት መንገድ ወይ ተጠቂ ይሆናል፤ ወይ ተከታይ ይሆናል። በስሙ ይነገድበታል፤ ወይንም ይወቀስበታል። ባልሆነ መንገድ ገብቶም ለጥቃት ይጋለጣል።

ማሕበረሰቡ እራሱን የሚገልጽበት የራሱ ግንዛቤ እና አረዳድ ቢኖሮውም፤ የራሱን መጠሪያም ሆነ ግንዛቤ ‘ነጥቀው’ “ሊሂቃኖቹ” በሚሰጡት ስምም ሆነ የአካባቢ ግንዛቤ እንዲታጠር ያደርጋሉ።ይህ

ድርጊት የሚፈጸምበት ምክንያት ለፖለቲካ፤ለሃይማኖትና ለስልጣን መቆናጠጫ ሲባል የሚከሰት ክስተት ነው።

የአማራን ደህንነት/ሴክዩሪቲ/ሴፍቲ የሚጻረሩ ሃሳቦች፤ ለሌሎች ጎሳ ሊሂቃኖችን በማቀበል፤ በማስረጃ ያልተደገፈ ፕሮፓጋንዳ ለጠላት በማቀበል ስማቸው የሚወቀሱ አማራዎች መሃል (አማራ አይደለሁም ቢሉም፤ ያንኑ አከብራለሁ) አንዱ ፕሮፌሰር መስፍን መሆናቸውን አዝኛለሁ።

ፕሮፌሰሩ አማራን በሚመለከት ሲተነትኑ፤አማራ የሚባል የለም ይላሉ። ለዚህ ደግሞ በቂ ትንትና ሲሰጡ አልሰማሁም፤ አላነበብኩም። አማራ የሚባል የለም እያሉ ለኢትዮጵያዊያን እና ለዓለም እየገለጹ ሲከራከሩ ቆይተው፤ “የለም” ሲሉት የነበረው “አማራ” የተባለ ማሕበረሰብ ደግሞ ከሃምሳዎቹ ዓ/ም ጀምሮ “አማራ” የሚባል ማሕበረሰብ እንደነበር ሳይታወቃቸው የራሳቸውን ሙግት እንደገና እራሳቸው ሲያፈርሱት “አቶ ተክሌ የሻው፤ ፕሮፌሰሩ” የጠቀሱት ማስረጃ ለማረጋገጥ ብዬ መጽሃፉን ገልጬ ሳነብበው እውነትም ፕሮፌሰሩ ሲሞግቱበት የነበረውን የእራሳቸው ነጥብ ተመልሰው ሲያፈርሱት ይታያል።

ፕሮፌሰሩ እንዲህ አይነት እራስን በራስ የመገራጨት/የመቃረንን ነገር የአፍ ወለምታ ነው እንዳይባል፤ በብዙ ገበሬ አነጋግሬአለሁ፤ ማስረጃ አለኝ እያሉ ነው የጻፉትና የሚከራከሩት። ይህ የራስን ትንታኔ በግልፅ ያለመተንተን አቋም ሌላውን ውዥምብር ውስጥ የመክተት አባዜ በእርሳቸው የተወሰነ አይደለም። የፕሮፌሰሩን የተምታታ ሐረግ እየመዘዙ፤የእሳቸውን ኮቴ እየከተሉ እራሳቸውን አምታትተው ሌለውን የሚያምታቱ የፕሮፌሰር ተከታዮች ብዙ ናቸው።

ለምሳሌ ከላይ የጠቀስኳት፤ ድሮ አገር ውስጥ ማሕበራዊ ነክ የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ነበረች የሚባልላት ዛሬ በእስተእርጅናዋ “ከልጆች” ጋር የጠላ ቤት ወሬ የሚመስል በፓልቶክ ክፍል ውስጥ ዘረኝነትን ስታቀማጥል፤ ወሬን እንደ እሳት እየሞቀችበት “እኔም ከዚቹ ቀን ጀምሮ ዘረኛ መሆኔን አንድታወቁልኝ” እያለች በካረንት አፌይረስ/ኢካዴፍ ፓል ቶክ ውስጥ አዘጋጅ ሆና የትግራይን ማሕበረሰብ በመዝለፍ የምናውቃት የግንቦት 7 “ካልት” የሆነቺው ወ/ሮ ብዙ ወንድማገኝ የተባለች ሴትዮ፤ “አማራ የሚባል የለም” ከሚሉት የፕሮፌሰሩ ተከታይ ነች።

የለም የማለት መብቷ ቢሆንም፤ የለም፤ወይንም አይደለሁም በሚለው ተወስና ዝም ብትል እኮ ባልከፋ፤ ሆኖም “አማራ አለ፤ ስለሆነም ተደራጅተን አማራን ከጨርሶ ጥፋት እንከላከል” ብሎ የተደራጀውን “ሞረሽ ወገኔ” የተባለው ፤ ’ሲቪክ’ ድርጅት፤ በመዝለፍ፤ አማራ የሚባል አለ የሚሉ ሁሉ ‘ለስልጣን ጉጉታቸውን ለማርካት ሲሉ ሊጠቀሙበት የተደራጁ ሰዎች እንጂ፤ የሌለን አማራ ለመከላከል እያሉ፤ በከፋ መልኩ ሊያስጨርሱት ነው” እያለች የሞረሽን መሪዎች እና ተከታዮች ባልታረመ አንደበቷ እየዘለፈች ስትወነጅል ትደመጥ እና፤ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ምላስዋን አጥፋ “እኔ ብመረመር ጥርት ያልኩ አማራ ነኝ ከጥፈሬ እስከ እራሴ” ፤በማለት እርስ በርስ የሚምታቱ አቋሞች ልክ እንደ ፕሮፌሰሩ የሚያንጻባርቁ ሰዎችን አድምጠናል። “የለም” ሲሉ ቆይተው አንደገና “አዎ አለ” ይሉናል። የቱን እንያዝ?

የህች ጋዜጠኛ ነበረች የምትባል ሴት የተናገረቺው አንደበቷን በሚቀጥለው ሰሞን እራሱ በቻለ በትችት መልክ እመለስበታለሁ። ስለሆነም የፕሮፌሰሩ የተሳሳተ ትምሕርት እንደ ወ/ሮ ብዙ

ወንድማገኘሁ በብዙ ሺዎች ሰዎች እርስ በርስ የሚምታታባቸው ተከታዖችን አፍርተዋል።

ጊዜው መቸም ቢሆን ጊዜው ለአማራው በከፋ መልኩ ነው እያንገላታው ያለው። ፕሮፌሰሩ የተምታታ አቋዋማቸው አይደለም ዋናው ትኩረቴ። አለ፤ የለም አይደለም። ትኩረቴ፤ ሕዝብን የማቃቃር ጽሑፋቸውን ላይ ነው ትኩረቴ። ልብ ማለት ያለበን፤ አማራ ነኝ የሚልም ሆነ አማራ አይደለሁም ብሎ እራሱን የካደ አማራም ሆነ ሌላው ወገን በአማራው ሕብረተሰብ ጥቃት ሲደርስ ዝምታን መምረጡ አሌ የሚባል አይደለም (ባለፈው ሰሞን ስለዚህ ጉዳይ በስፋት ገልጫለሁ) ከሊቅ እስከ ደቂቅ አማራ በልጆቹ የተከዳ ማሕበረሰብ ነው። ፕሮፌሰሩ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ስለነበሩ በጎ ስራ ሰርተዋል። ወቀሳው እሳቸውን አይመለከተም (እኔ እስከተረዳሁዋቸው ድረስ)። ከወቀሳ ነፃ ያላደረጋቸው ግን አንድ ነገር አለ። ወደ ታች እንመለከታለን።

በዚህ በወያነ ትግራይ ዘመን ለ24 አመት አማራው ጥቃት እየደረሰበት ይገኛል። ፕሮፌሰሩ “አማርኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ አይደለሁም” ወይንም እየተጠቃ ያለው አማርኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ አይደለም። አማራ የሚባል የለም፤ እያሉ ስለ አማራ ሕብረተሰብም ሆነ ስለ እራሳቸው ማንነታቸው የሚናገሩት “ሂፕክሪት/ዶግማ/ ግትር” ክርክራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ አማራ የተባለ ማሕበረሰብ አማራ በመሆኑ ብቻ እየተጠቃ ፤እየተባረረ መሆኑን እሳቸውም በውስጠ ሕሊናቸው የሚክዱት አይመስለኝም።

አማራን ለማጥፋት ”በኦጋዴን ሶማሌ ክልል” ውስጥ አማራን በሚጠሉ ሶማሌዎች እየተሰነዘረ ያለው አማራን የማባረርና የመግደል ወንጀል” ከመመከት ይልቅ “ወያኔዎች፤ኦጋዴን ነፃ

አውጪዎች፤አነጎች......የመሳሰሉ የፋሺስት ድርጅቶች” አማራን ለማጥፋት የሚፈልጉት ብትርና መሟገቻ ሃሳብ በማቀበል ለፋሽሺስቶቹ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ “አማራን በሃላፊነት የሚያስጠይቅ፤ የሚጎዳ ጽሑፍ” ወያኔ ከገባ በኋላ ጽፈው ለጠላቶች አበርክተዋል። ያውም በመጽሐፍ ውስጥ ታትሞ የሚነበብ! ይህ ለምን ሆነ?

ከፕሮፌሰሩ ጋርም አብሮ፤ አማራው ገበሬ ዛሬ በአማራነቱ ብቻ ለመጠቃቱ ክስተት መነሻና ቆስቋሽ ሰበቦች የስታሊናዊ/ የማኦ/የማርክስ/ሌኒን የፖለቲካ ንዳድ ያበሰለው “ጫፍ የረገጠ/አክራሪ/አልትራ/ኤክስትሪም” ግራ ዘመም አቀንቃኝና በአማራው ማሕበረሰብ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ሲያካሂድ የነበረ የ70ቹ የተማሪ ማሕበረሰብም አብሮ ተጠያቂ ነው።

ይህንን ስናነሳ በግምባር ቀደም የሚታወሰው ሟቹ የቀ/ሃ/ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ዋለልኝ መኮንን ነው። ወጣቱ ዋለልኝና ፕሮፈሰሩ በአማራ ላይ ሲመሰክሩ፤ ከአንድ እናት የወጡ “መንትያዎች” ይመስላሉ። ትግርኛው **“ክናናን- ምናናን”** ይላቸዋል። መንተያዎች ማለት ነው።

በቅርቡ በሞረሽ ሊቀመንበር በአቶ ተክሌ የሻው የቀረበው **./ ለፕሮፌሰር መሥፍን የመጽሐፍ ምረቃ ታዳሚዎች እና ለእርሳቸው አድናቂዎች በሙሉ፤**............ የሚል ለፕሮፌሰር መስፍን ያቀረቡት የጽሑፍ ጥያቄ፤ ፕሮፌሰሩ መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። አቶ ተክሌ የሻው ፕሮፌሰር መስፍን ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ የጻፉትን ጥቅስ መነሻ ያደረጉትን ልነሳ፡
“ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም፡-

«ሥልጣን፣ ባህልና አገዛዝ፤ ፖለቲካዊ ምርጫ» በሚል ርዕስ በ2003 ባሳተሙት መጽሐፈዎ ገጽ 120 ላይ እንዲህ ብለዋል።

«ኅዳር 1951 ዓም ከአጼ ኃይለሥላሴ ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ባለሥልጣኖች ባሰራጩሁት የጥናት ጽሑፍ ስለኦጋዴን የሚከተለውን ብየ ነበር። «በጠቅላላው የአማሮቹና የሱማሌዎቹን ግንኙነት ላስተዋለው፣ አማራዎቹ የሚያሳዩት የበላይነት መንፈስና በሱማሌዎቹ ላይ ያላቸው ንቀት፤ ሱማሌዎቹ በበኩላቸው ያላቸው ኩራት በአማራዎቹ ንቀት እየተነካባቸው የሚሰማቸው ስሜት በአንዴ ይታወቃል። ``ቆሻሻ ሱማሌ``በያለበት የሚሰማ ነው። በዕድሜም ሆነ በክብር ከፍ ያሉትን ሱማሌዎች እርሰዎ እያለ የሚያነጋግራቸው በቁጥር ነው።---እንደዚህ ዓይነቱ የሌለውን የአማራ የበላይነትና የሱማሌ የበታችነት በግልጽም በድብቅም የሚያሳይ መንፈስ የሱማሌዎቹን ልብ በጣም እንደሚያሞክረው የሚያጠራጥር አይደለም። ሱማሌዎቹ ልክ እንደአማራዎቹ መሆናቸውን ሁሉ የተገነዘቡት አይመስሉም፤ ሱማሌዎቹም ሁሉ የሚውቁት አይደለም።» ..................................................”

( መስፍን ወ/ማርያም «ሥልጣን፣ ባህልና አገዛዝ፤ ፖለቲካዊ ምርጫ» በሚል ርዕስ በ2003 ባሳተሙት መጽሐፈዎ ገጽ 120)

አቶ ተክሌ እንዳሉት ፕሮፌሰሩ ከምን ጥናት ነስተው ነው ዛሬ አማራ በጅምላ እየተገደለ ባለበት ወቅት እንዲህ ያለ ውንጀላ ሊወነጅሉት የተነሱት በምን መነሻ ነው? የሚል ጥያቄ ይቀሰቅሳል። አሁን አማራው በገፍ እየተገደለ ባለበት ጊዜ እውን ከአንድ ምሁር

የሚጠበቅ ነው? አማራው ብትር በበዛበት ሰዓት መወንጀሉ ጥቅሙ ምንድ ነው?
ሽመገሉ እንዳልል፤ ኣእምሮዎ ከወጣት አእምሮ በተሻለ የሚሰራ መሆኑን የሚያጠያይቅ አይደለም። ቢያምኑትም ባያምኑትም፤ ወያኔም ሆኑ ሶማሌዎቹ አማራን ለማዋከብ የእርስዎን ድጋፍ በእጅጉ ይፈልጉታል።ዋለልኝን እንደ አርበኛ የሚቆጥሩት ወያኔዎች፤ ሻዕቢአዎች፤ ኦነጎችና ኦጋዴን ሶማሌዎች ይህንኑ አርስዎ የሰነዘሩት ውሸት እየዋሸ አማራውን መሰረተ ቢስ በሆነ ክስ በመወንጀሉ ነው የሚያከብሩት። ዋለልኝም ሆነ እነኚህ አገር በቀል ፋሺስት ግልገሎች፤ጣሊያኖች ያቀበሉዋቸውን የሃሰት መረጃ ነበር ተቀብለው አማራውን ሲወነጅሉ የኖሩት። ለርስዎ አይንት ሊቅ የተደበቀ ታሪክ አይደለም።

በአማራው ላይ የጥላቻ ትኩረት እየተደረገበት፤ ሂደቱ እያደገ የመጣው፤ ከውጭ በኩል በውጭ ጠላቶች የተነዛ አገር ማፍረሻ መረጃ፤ ከአገር ውስጥ ደግሞ ዋለልኝና መሰሎቹ ያደለቡት ውሸት ሥር ሰድዶ ‘አማራ’ ለዚህ ጥቃት ተጋልጣል። እርስዎ ለሶማሌ ኦጋዴኖች በሰጡዋቸው ምስክርነትዎ እና ዋለልኝም ደግሞ “ብሔር፤ብሔረሰብ....ሕዘቦች” ብሎ አገር ለመበተኛ እንዲያመች በኮሚኒስት አጠራር ለሰየማቸው የኢትዮጵያ ነገዶች በጸረ አማራ ሃይላት ምስክርነታችሁ ቢሞገስም፤ በማይፋቀው የታሪክ ማሕደር “መንትያዎች” ሆናችሁ ተመዝግባችኋል።

በትግርኛ አንድ ምሳሌ አለ፡ “አድጊ ተማህሊላ በላዒዓ አምጺኣ” ( አህያ ጮሃ ጮሃ የሚበላትን ጅብ አመጣች)፤ እርስዎ አማርኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ አይደለሁም ቢሉም፤ ወያኔም ሆነ የወያኔ ሎሌዎች በየፓልቶኩ እርሰዎንም የሚያየውና የሚጠራው በነፍጠኛነት ነው። ወያኔ አማራን በሚመለከትበት መነፅር

እርስዎንም አብሮ ያይበታል። ስለሆነ እርስዎም በሞላ ጎደል የወያኔ ተጠቂ እንደሆኑ የሚካድ አይደለም (ስለ እርስዎ ወያኔ ትግሬ፤ ጸሃፊዎች በትግርኛ ቋንቋ የሚጽፉት እና በራዲዮናቸው የሚንዘላዘሉበት ባለጌ ምላሳቸው ቢያነቡና ቢያደምጡ ኖሮ፤ ምንኛ በአማራ አንደተመደቡ ያውቁት ነበር)። እስኪ የእርስዎን እና የዋልልኝን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ለሶማሌ አጋዴኖች ያቀበላችኋቸው ብትር ስራ ላይ ውሎ ተተርጉሞ ፍሬ አፍርቶ ምን ውጤት አንዳሰስገኘ ከዚህ በታች ያለውን እንመልከት፡

ክቡር ፕሮፌሰር ሆይ!

ወያኔ ከትግራይ በረሃ ገስግሶ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ የሽግግር መንግስት ተብየው ሲመሰርት፤ የተሰነዘረን ንግግር እርስዎ አይስቱትም። ለአንባቢዎቼ ላስታውስ "አማራና ኦርቶዶክስን እንዳያንሰራራ አከርካሪውን ሰብረነዋል" በሦስቱ ቀለማት መሃል ነጭ መስመር ሆኖ ከመሃሉ ጥቁር ቀለም ይሰመርበት!"... "ጠላታችን ከባንዲራው በስተጀርባ ያለው ክፍል ነው" .... "ነፍጠኛው ይህንን ባንዲራ እያውለበለ..." "ይህ ጨርቅ!..." እያሉ በዕብዶች አዳራሽ ላይ ዕብዶች በብሔራዊ ሰንደቃላማችንና በአማራው ላይ የሰነዘሩትን ንግግር ምን ይሉ አንደነበር ሰምተናል።

ዛሬ ደግሞ በቅርቡ ከአንድ አመት ተኩል በፊት ማለትም በ2014 ዓ.ም እንደ ጎርጎርዮስ ዘመን አቆጣጠር ቅድመ አያቶቻቸው የኖሩበት፤ እንዲሁም ባለፉት አርባ እና ሐምሳ አመታት በጅጅጋ ከተማ ሲኖሩ የነበሩ የጅጅጋ የአማራ ማሕበረሰብ ኗሪዎች ለኢሳት የጻፉትን ደብዳቤ ልጥቀስለዎት፡-

እነኚህ ማሕበረሰቦች በሶማሌዎች እደረሰባቸው ያለውን የማባረር ዘመቻ እና ሌሎች የግፍ ተግባሮች እየተከታተለ አገር ውስጥ የሚያስተጋባላቸው የጋዜጣም ሆነ የራዲዮ ድርጅት ወይንም የፖለቲካ ተቃዋሚ ባለመኖሩ ፤ በ2014 እንደ አውሮጳ አቆጣጠር የጅጅጋ ኗሪዎች የሆኑት አማራዎች፤ ዋሺንግተን (አሜሪካ) እና አምስተርዳም (አውሮጳ) ውሰጥ ለሚገኘው በውጭ አገር ሃይላት የገንዘብ ዱጎማ ለሚንቀሳቀሰው "ኢሳት" ለተባለው ሻዕቢያዊው የግንቦት 7 ራዲዮና ቴ/ቪ የጻፉትን ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

( " ቤታችን እየተነጠቅን ለጎዳና ተዳዳሪነት ተጋልጠናል። እስካሁን ድረስ በከተማዋ ውስጥ የነበሩት የአማራዎች ዋና ዋና የንግድ ተቋማትን እየተነጠቁ ለሶማሌ ተወላጆች እያስረከቡ ስለተደረገ አብዛኛዎቻችን ከተማውን እየለቀቅን ወደ መሃል አገር ሄደናል።

ተወልደን ያደግንበትን አገራችን አንለቅም ያሉትንም ፌደራላዊ ጫናዎች እየተደረጉ ከተማዋን ለቅቀው እንዲወጡ በደብዳቤና በቃል ትዕዛዝ ተነግሯቸዋል።

የአንድ ቤሔር የበላይነት በሰፈነበት መልኩ "አማራ ወይንም ሐበሻ" የሚል መጠሪያ ተደርጎልን፤ እነሆ ከህጻናት እስከ ትልቅ በመንገድ በቢሮም እየተሰደብን መኖራችነን ሳያንስ፤ አሁን ደግሞ ያለምንም ልዋጭ ቤቶቻችን ተቀምተን ሜዳ ላይ ተጥለን እንገኛለን።

የኛ ልጆች አንደልብ መንገድ ላይ መሄድ አይችሉም፤ ሱሩ የለበሰች ሴት 'አማራ ነች' እየተባለ በፖሊስ በዱላ ትደበደባለ፤ች። ማን ፖሊስ ማን ሃላፊ እንደሆነ በማናውቀው ሁኔታ የ "ሸሪዓ ፍርድ ቤት" ተቋቁሞ ቤቶቻችን እንድንለቅ እየተደረገ ነው። ተወልድን ባደግንበት አገር አንደ ሁለተኛ ዜጋ እንደ ቆሻሻ እየታየን ነው ብለዋል።"

አንድ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ የከተማዋ ኗሪ በከተማዋ የመኖር ስሜታቸው እየተሟጠጠ መሄዱ ደግሞ በስልክ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል።

"በዚህ አካባቢ የመኖር ስሜታችን ተሟጥዋል። ያፈራነውን ያለንን ነገር ለቀቅቀን ለመውጣት እየተዘጋጀን ነው። ሰላሳ እና አርባ አመት እና ከዚያም አመታት በላይ የኖርክብትን ቦታ ለቅቀህ ስትሄድ ዝም ብለህ ወፍ አይደለህ፤ በርረህ አትሄድም። አንዳንድ ያፈራሃቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ልጆች ይኖራሉ..አንዳንድ ንብረቶች ይኖሩሃል... እነሱን ጥለህ አትሄድም፤ አጋጣሚና ዕድል ይገኝ እንደሆነ ብለን፤ አንዳንዶቻችን ያንን እንደምንም ብለን እያስተካከልን ብለን ነው እስካሁን እየተንገዳገድን ያለነው። የወደፊት በዚህ ከታማ የመኖሩ ተስፋ እንኳን እንጃ!..እንጃ!" )

ሲሉ አማራዎች እንደ ሶማሌ እስላም "ሸሪዓ ፍርድ ቤት" ቀርበው ንብረታቸው እያስረከቡ ወደ አገራችሁ ሂዱ እየተባሉ እንዲባረሩ ሲወሰንባቸው; ልጃገረዶች ልጆቻቸውም "ሱሪ" ታጥቃ ስትሄድ እንደ ሳውዲ አረቢያ "**ስፋጢን**" ተብለው በሚጠሩ የሃይማኖት ፖሊሶች "አማራ/ሐበሻ" እየተባሉ በዱላ ይደበደቡ እንደነበር አማራዎች በጅጅጋ የደረሰባቸውን ግፍ አስረድተዋል።

ከዚህ ሌላ የኦጋዴን ሶማሌ ክልል ፕረዚዳንት ተብየው ጸረ አማራ ዘመቻ በማካሄድ፤ የአካባቢው ስማግሌዎችን ሰብስቦ፤ አማራ የሚባል ጠላታችን ነው "ትግሬዎች" ወዳጆቻችን ናቸው፤ እያለ ሶማሌዎች አማራውን እንዴት ማባረር እንዳለበትና፤ ማጥቃት እንዳለባቸው የቀሰቀሰበትን፤ በአውዲዮ ቪዲዬ የተቀረጸውን ማስረጃ ይህንን ይመልከቱ'-

TPLF puppet Somali president secret video exposed TPLFs hate against Amhara May 8 2013
https://youtu.be/Kj2sNJ5B2j0

እንግዲህ ክቡር ፕሮፌሰር መስፍን ይህ ግፍ ሲፈጸም በመጽሐፍዎ የዘገቡት በመረጃ ያልተረጋገጠ አማራውን የመወንጀል ዘመቻዎ የአካባቢው የፖለቲካ የፋሺስት ግልገል ድርጅቶችና እና የአካባቢው አክራሪ እስላሞች በአማራው ሕብረተሰብ ላይ ያነጣጠረ የተቀነባባረ ጥቃት ልክ አንደ እነ "ታምራት ላይኔ" ንግግር ለዛሬው ግፍ የእርስዎ ምስክርነት ተጨማሪ ብትር አላቀበልኩም ሊሉ ይችላሉ?

**ዋለልኝ መኮንን**



ይህ ፎቶግራፍ በዋናነት የተዘገበውና ድረገጽ ላይ እንዲሰራጭ ያደረገው በቅድሚያ ስያትል ለሚኖረው ለዋለልኝ ጓደኛ ለአቶ ዘውገ ፋንታን አመሰግናለሁ (በሁለታችን መሃል የከረረ ቅራኔ ያለን ቢሆንም ንብረቱ ነውና ምሳጋና አቀርብለታለሁ)። ይህ ካልኩ ዘንድ፤ ይህ ወጣት እጅግ መረን የለቀቀ ግራ ዘመም ፍልስፍና ያጠቃው፤በራሱ ላይ እና እሱን በፈጠሩ የአማራ ማሕበረሰብ ላይ መሰረተ ቢስ ውንጀላ በመሰንዘር፤ የኢትዮጵያን አንድነት ለመበተን፤ የዘር ጽዳት ለማካሄድ ታጥቀው የተነሱ አክራሪ ሃይላትና በታኝ/ኒሂሊስት ቡድኖች እንዲሁም እንደ እነ ወያኔና ኦነግ የመሳሰሉ ግልገል ፋሺስቶች፤ የዓላማቸው መሪ ተዋናይና ታላቅ ሰማዕት አድርገው በክብር የሚያዩት ወጣት ነው።

የዚህ ወጣት ታሪክ በጓደኛው በዘውገ ፋንታ የተዘገበው ዘገባ የሚያመለክተው (የወቅቱ ወጣቶች አብዛኛዎቻችን ዋለልኝ በወቅቱ ማን መሆኑን የምናውቅ ብንኖርም) ዋለልኝ በአዲስ አበባ ዩኒበርስቲ ማህበርና (USUAA) በብሔራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር (NUEUS) ከፍተኛ አመራር አባል ሆኖ ። የወቅቱ ማርክሳዊና ሌሊናዊ ግራ ዘመም የፖለቲካ አቀንቃኝ ዋና ነበር። ዋለልኝ ከነ ማርታ እና ጀብሃ ከላካቸው አንዳንድ ሰዎች ጋር ሆኖ በ1965 ዓ.ም ወደ ውጭ አገር አይሮፕላን ጠልፎ ለመውጣት ሲሞክር በጸጥታ ሃይሎች በጠለፋው ግብግብ ሰማይ ላይ እንዳለ ሕይወቱ አልፏል።

ለጠለፋው መነሻ ጓደኞቹ እንደሚሉት "ጀርመን በርሊን ውስጥ የኢሕአፓን ስብሰባ ለመካፈል ወይንም በዛው ለመቀላቀል፤ ከአገር የሚወጣበት መንገድ ስላጣ አማራጭ ስላልነበረው አይሮፕላን ጠልፏል። ሲሉ ሃሳባቸው ይገልጻሉ። ሆኖም እኔ ከኤርትራ የጀብሃ ፋይሎች እንደተረዳሁት ግን ፤ የጠለፋው ቀስቃሽ ፕላን የተቀነባበረው በኤርትራኖች እንደሆነ ነው። ከነ ዋለልኝ እና ማርታ መብራቱ.....በጠለፋው የተሳተፈው "ራዲዮ" እየተባለ በጀብሃ የቅጽል ስም የሚታወቅ ሕጋዊ ስሙ "ሳሙኤል ዮሃንስ" ቢሆንም ስሙን በመቀያየር ታደሰ መሐመድ፤ዑስማን መሓመድ በመባልም ይታወቃል፤። ይህንን ለማወቅ እኔ በኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ በጻፍኩት፤ ከዚህ በታች ልጥቀስ፤-

"ወደ ሊቢያ በተካሄደዉ ጠለፋ ተሳታፊ ኖሮ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ከገረግር -ሱዳን በረሃ የአይሮፕላን ጠለፋ ለማካሄድ ታዝዞ፤ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ በመሄድ በንግድ ሥራ እየተሰማራ የሚኖር በማስመሰል ዋለልኝን በፍቅር ያኖሆለለችዉን መልከመልካምዋ "ፍያሚታ-ጊላይ" (በማርታ መብራህቱ) በኩል

ዋለልኝን ለጠለፋዉ ስራ እንዲስማማ እና ጃንደረባዎቹም እንዲቀላቃሏቸዉ በማድረግ የተገንጣዮቹን የጠለፋ ስራ ለኤርትራዊያኖች ጥቅምና ተጨማሪ ሃይል እንዲሆኑ አድርጓል። ጠለፋዉ ከተከናወነ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ጠላፊዎቹ እነማን እና ለምን አላማ እንደነበር ተገንጣዮቹ ባስተላለፉት የራዲዮ መልዕክት በወቅቱ ተገልጿል። አማኑኤል ዮሃንስ ለማን እየተጋለ እንደነበር ማን እንደላከዉ ከዛ በፊት በሊብያዉ የጠለፋ ተልእኮ የተሳተፈ መሆኑን በጠለፋ ስራ መስማራቱን ዋለልኝ በሚገባ ያዉቃል።ሃሎ!!!!ሡሩሩር!!!!

በዋለልኝ ዙርያ የነበሩ ኤርትራዊያን ጃንደረባዎቹ አብዛኛዎቹ "ህዝባዊ ሓይልታት (ቡድን 2) ተብሎ የሚታወቀዉ የኢሳያስ ተከታዮችና ተዋጊዎች ነበሩ።በጠለፋዉ ወቅት የተሰማሩት 3 ኤርትራዊያኖች እና 4 ኢትዮጵአዊያን ነበሩ።ማርታ መብራህቱ፤ አማኑኤል ዮሃንስ ( "ራድዮ") እና ዮሃንስ ፍቓዱ። በዚህ በኩል ደገሞ ዋለልኝ መኮንን፤ጌታቸዉ ሃብቴ ፤ተስፋየ ቢረጋ፤ታደለች ኪዳነ ማርያም። ነበሩ።....አማኑኤል ዮሃንስ (በሁለተኛዉና በሦስተኛዉ ዙር ጠለፋ ከነ ዋለልኝ የተሳተፈዉ ነዉ)ደበሳይ ገብረስላሴ፤ ሙሴ ተስፋሚካኤል፤ ዮሃንስ ስብሃቱ፤ ሙሴ ተስፋሚካኤል (አይሮፕላናችንን ጠልፈዉ ሊቢያ የገቡ ናቸዉ)። ዮሃንስ ስብሃቱ እና ሙሴ ተስፋሚካኤል በ1973 (ፈረንጅ) በተነሳዉ የዉስጥ አመጽ/እንቅስቃሴ (መንካዕ- ተብሎ በሚታወቀዉ የኢሳያስ የአፈና አርምጃ እነደተገደሉ ይታመናል።)"

ዋለልኝ ከነበረው እውቀትና ገናናነት እና ማርክሳዊ ርዕዮት ከጸረ አማራዎቹ ከኤርትራኖቹ ጋር ሚስጢርም ሆነ ግንኙነት በግሌ የሚያውቀው ነገር የአልነበረውም ማለት አይቻልም። ምክንያቱም

የእጅ በምብና ሽጉጥ የመጣው ከአስመራ በኤርትራኖች በኩል እንደሆነ አንዳንድ ምንጮች ያመላክታሉ።” መረሳት የሌለበት ማርታ ኤርትራዊት ነች፡ የጀኔራል መብራህቱ ጎይተኦም ልጅ ነች። እስከዛሬ ድረስ ወንድሟ የሻዕቢያ ተሞዳሟጅ ነውም ይባላል።” (ምንጭ የራሴው/ኢትዮጵያን ሰማይ)

እሷም እንዲሁ በዛው ወቅት የለችበትም ማለት ትንሽ የዋህነት ያሰኛል። ግንኙነቱ ምናልባትም በማርታ በኩል ዋለልኝን ማሳመን ሊሆን ይችላል። የቅርብ ጓደኛ ስያትል የሚኖሮው ወለየው ዘውገ ፋንታ ስለ ጓደኛው ዋለልኝ እንዲህ ሲል “Martha was a beautiful woman, but extremely uptight. She was the only person I could not break into laughter. If Wallelign walked to the bathroom or to the kitchen, she would stand and look. The first day I saw her with Wallelign, I asked him if she were his girl friend. He smiled and said: “Ziga.” በጽሁፉ ነግሮን ነበር።

ስለዚህም ዋለልኝ በአማራ ላይ ያሳደረው የተዛባ አመለካከቱ፤ ከሴት ጓደኛው ከማርታ ጋር የነበረው ንኪኪ ሳይጎትተው እንዳልቀረ እገምታለሁ። በወቅቱ ክስ ሲመሰረት፤ ማርታ በወቅቱ የቀ.ሃ/ሴ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ኮለጅ ተማሪ እንደመኖሯ ሁሉ፤ አይሮፕላን በመጥለፍ ለኤርትራ ነፃ አውጪዎች በሕክምና ፈቅዳ ለማገልገል እንደነበር፤ የታሪክ ምንጮች ከተከሰሰችበት ማሕደር ያገኙትን ይጠቅሳሉ። ልብ ማለት የሚኖርብን በረራው ከተጠለፈ በኋላ የኤርትራ ነፃ አውጪ ድርጅት ወኪል የጠለፋው ምክንያት

ለኤርትራው ቡድን ድጋፍ ለመስጠት እንደነበር ከሊቢያ መግለጫ ሰጥቶ መኖሩን ልብ በሉ።

ያም ሆነ ይህ፤ ኤርትራኖች ዛሬም አሽከር አላጡም። የኢሳት ጋዜጠኞችም ሆኑ ግንቦት 7 የተባለው ድርጅት ሻዕቢያን ለማሞገስ በወያኔ እግር ለመተካት ብቅ ብሎ ወገቡን አለጥልጦላቸዋልና ከጠላት ጋር የመሞዳሞድ ክስተት ለታሪክ ማሕደር እንተወው። አሁን ኤርትራ ምድር ውስጥ ሆኖ የእነ "ፍረወይኒ" የቡና ጣዕም በማድነቅ እየጻፈ ያለው፤ ኤፍሬም ማዴቦ፡- *"ነፍጠኞችን ቁጥጥር ሥር አድርገንላችኋል"* ብሎ ለሻዕቢያ "ፌስቲቫል" ተሰብሳቢዎች ኦክላንድ ካሊፎረኒያ ውስጥ በአንደበቱ አረጋግጦላቸዋል። ይህች ቡቹላ ካሁኑ እንዲህ የጮኸች ስትድግ .......!!!!! ምን አንደምታደርግ አያሰኛችሁም?

ይህንን እንለፈው እና፤ ዋለልኝ አማራ ሆኖ አማራውን በጅምላ የሚወነጅል እጅግ አደገኛ "አልትራ" (ያልተገራ) ርዕዮት ሲያስፋፋ የነበረ unfairly/ ከምክንያታዊ ውጭ በሆነ መንገድ አማራን የወነጀለና ጥላሸት የቀባ ወጣት ነበር።

**ምኒሊክ ሳልሳዊ** ተባለ የግንቦት 7 ጸሐፊ እንዲህ ይላል።

"ዋለልኝ መኰንን በአንዳንድ ግለስቦች እንደ ተራ አውሮፕላን ጠላፊ ቢታይም በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት በተደረገው ትግል ታሪክ ውስጥ ያደረገው ግንባር ቀደም ተሳትፎውና የብዕሩ ለዛ ሚዛናቸው የደፋ ነው።" ይላል።

እርግጥ ዋለልኝ ጠንካራ ጸሐፊ ነው። ለዛነቱ ምን ላይ እንደሆነ ባይገባኝም፤ ዋለልኝ ሲጽፋቸው የነበሩ ጽሑፎች ከትምህርቱ ደረጃ አኳያ እጅግ የመጠቁ እንደነበሩ አይካድም። ከጽሑፎቹ መካካል

አንዱን በምሳሌ ብንወስድ ለዛ ያለው ሳይሆን ለዛ ቢስ የሆነ አማራውን ሕብረተስብ የሚወነጅል፤ለዛሬው የአማራ ሕብረተሰብ ስቃይ ከፍተኛ ብትር ያቀበለ "አናካሽ" ጸሐፊ ነበር (ነብሱ ይማረው፡ ከይቅርታ ጋር! ታሪክ ትቶልናል እና እንነጋገርበታለን። እየተነጋገርን ያለነውም ከእርሱ ጋር ሳይሆን የሱን ማሕደር የተሸከሙትን እና በመንገዱ የተከተሉትን ሻዕቢያዎች፤ወያኔዎች፤ ኦነጎችን እና ወዘተ...ድርጅቶችን ነው)።

አማራን በመዝለፍ የታወከቀው የወያኔው አማርኛ ተናጋሪው ክፍል የብአዴን ድርጅት አመራር አባል **"አለምነው መኮንን"** የተባለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሳይጨርስ ወደ ወያኔ አሽከር ወደ ብአዴን ድርጅት ተቀላቅሎ፤ ዛሬ ስልጣን ተሰጥቶት አማራውን **"አማራ በባዶ እግሩ እየሄደ በስንፋጭ ትምክሕት የታጀለ መርዝ ንግግሩን እስካሁን ድረስ ማቆም ያልቻለ፤ትምክህት እየተመገበ ያደገ፤......**እያለ "የብአዴን ሁለተኛ ሰው" የሆነው ባሕርዳር ውስጥ ተቀምጦ የተናገረው ዘለፋ፤ በእኔው ድረገጽ በኢትዮጵያን ሰማይ ላይ **"የአመቱ ባለጌ ሰው ተብሎ"** የተሰየመው አለምነው መኮንን እና ዋለልኝ መኮንን እንደ አጋጣሚ ሁለቱም "ወሎየዎች" ናቸው። ባለመታደል ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ልጅ አባቱን ይዘልፋል፤ ይክዳል የሚባልበት ውቅት አለ። እነኚህም ለዚህ ምሳሌ የሚመቹ ናቸው።

የነ አለምነህ መኮንን አማራን የመዝለፍ የቅጥረኛነት ባሕሪ ሲሞገስ ሰምተናል። **"ሲሳይ መንግሥቴ አዲሱ"** የተባለ የብእዴን ታጋይ የነበረ ዛሬ በወያኔ ሥርዓት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሕግ እና የፌደራልዝም መምሕር የሆነው ግለሰብም፤ ዘለፋው **"ወርቅ የሆነ አባባል"** ሲል አማራን መስደቡን ደግፎታል።

ወደ ዋለልኝ ስንመለስ፡ ሕዳር 10/1961 በታታመው “ታገል በሚባለው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መጽሔት ላይ ‘የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ’ (On the Question of Nationality in Ethiopia) አማራውን ክፉኛ ወንጅሏል። ባገሪቱ ውስጥም የመድብ ትግል ሳይሆን ዋነኛው ጥያቄ የብሔር ጥያቄ ችግር ነው፤ በማለት ማርክሳዊ አመለካካቱን በማስፈር ጨቋኛም “አማራ ብሔር” ነች ሲል ይከራከራል።

ይህ በዚህ የተሳሰተ አባባሉ ሳይገታ ዋለልኝ የገዛ አገሩ “ፌክ ኢትዮጵያ፤የአማሮች ኢትዮጵያ.....” ይላታል። እርሱ አማራ ሆኖ “ኢትዮጵያን የአመሮች ንብረት ነች! ኢትዮጵያዊ ለመሆን መታወቂያዉ የአማራን ስም መያዝ ነዉ” ፤ካልሆነ ዜግነትህ አይከበርም፤ አይታወቅልህም” እያለ የነዛዉ ጸረ-አማራ ዉዥምብርና የውሸት ፕሮፖጋንዳዉ ከኤርትራዊያን ተጨምቆ ወደ እሱ ተላልፎ እንደ ራሱ ቅባት ሲጠቀምበት የነበረው ጸረ አትዮጵያ አፍራሽነቱ መረን የለቀቀ ነበር።

በጽሑፉ እንደተነተነው ግን የኤርትራኖች ትግል እንደ ኮለኒ የተመለከተው አልመሰለኝም። እሱ ሚለው የብሔረተኛ ትግላቸው በወዝ አደርና ዓለም አቀፋዊ እይታ ያላቸው ሰዎች ሳይሆን በከበርቴዎች እና በአካባቢ ባለርስቶች የተመራ ስለሆነ ትግላቸው ከእኛው ጋር አይሄድም፤ ስለሚል ስለ ኤርትራ ግልጽ አቋም አላስቀመጠም። እንደተረዳኝ ከሆነ።

ዋለልኝ ብርቱ አንጎል እንደነበረው በምንም መልኩ የሚካድ አይደለም። ሆኖም ያ ብርቱ አንጎል አማራ ላይ ሲደርስ ፍርስርሱ የወጣ ብቻ ሳይሆን አማራን በሃሰት በመወንጀሉ እጅግ አስገራሚ ክስተት ነው። ምናልባትም ወደ እዛው ሊያመራው ያስቻለው

*መንገድ ብዬ የምጠረጥረው ማርታ ግንኙነት ይሆን? ትግሬው የፍቅርን ምንነት ሲገልጽ "ፍቕሪ ዑውር" ይለዋል (ፍቅር ዕውር ነው) ፍቅር የወንድ እቅጣጫን ያሳስታል፡ መጽሐፍ ቅዱስም ተናግሯል።ሃይለኛ ፖለቲከኛ እና ሽፍታ በሴት ይማረካል። ሌላ ምክንያት ይኖሮው ይሆን? መልሱ ለታሪክ እንተው እና፤-*

On the Question of Nationality in Ethiopia- by Wallelinge Mekonnene Arts IV, HSIU Nov. 17, 1969 **ብሎ ሳላመነታ ለክርክር (ፕሮቮኬሺን) አቅረቤዋለሁ ያለለትን ወረቀቱ እንዲህ ይላል፡- "አደራ የምላችሁ ከጽሁፌ ውስጥ ሐረግ /አረፍተ ነገር በመምዘዝ ከዋናው ተልእኮ በመነጠል የማይሆን ትርጉም ከመስጠት ተቆጠቡ" ይላል። ዋለልኝ ይህን ይበል እንጂ በአማራ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ባስተዳዳር ቢበደልም መስዋእት ለመሆን ሲሽቀዳደምላት የነበረው ሕዝቧ "ኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜቱ የውሸት ነበር" "ምንም አልነበረውም" ሲል የሰነዘረው መሰረተ ቢስ ውንጀላው ሐረግን በመምዘዝ መተርጎምና መጠምዘዝ አላስፈለገኝም። መልዕክቱ ቀጥተኛ እና ግልጽ ስለሆነ ስለ አማራ እና ኢትዮጵያ ምን ብሎ አንደጻፈ/እንደተከራከረ አሳያለሁ። ላሰምርብት የምፈልገው ጉዳይ ግን "ዋለልኝ አገሩ አይወድም" የሚል ክርክር አይደለም እየተከራከርኩ ያለሁት። እያልኩ ያለሁት ጠንካራ አገር ወዳድ ሆኖ እያለ፤ ዘመናይ አስተዳዳርና ፍትሕ ፈላጊ ቢሆንም፤ ስለ አማራ እና በገዛ አገሩ የነበረው ግንዛቤ የተበረዘና ጠንከር ባለ ቃላት ልጠቀምና "አገሪቱን ለብጥብጥ የሚያነሳሳና የተመረዘ" መርዘኛ እና በታኝ አቅጣጫ የሚያራምድ ነበር ነው አባባሌ።**

**ፕሮፌሰር መስፍን እና ዋለልኝ ልዩነታቸው "ፕሪፌሰሩ" አማራ የሚባል የለም ሲሉ፤ ዋለልኝ ደግሞ አማራ የሚባል አንደነበር ነው**

በወቅቱ ግልጽ ያደረገው። ያ ካልሆነ አማራን በመወንጀሉና ጥላሸት በመቀባት ረገድ ልዩነታቸው ብዙም አይራራቁም።
ዋለልኝ እንዲህ ይላል፡

“…. the Question of Nationalities-some people call it ridiculously tribalism-but I prefer to call it nationalism.”

“….What are the Ethiopian people composed of? I stress on the word peoples because sociologically speaking at this stage Ethiopia is not really one nation. It is made up of a dozen nationalities with their own languages, ways of dressing, history, social organization and territorial entity.

“And what else is a nation? It is not made of a people with a particular tongue, particular ways of dressing, particular history, particular social and economic organization? Then may I conclude that in Ethiopia there is the Oromo Nation, the Tigrai Nation, the Amhara Nation, the Gurage Nation, the Sidama Nation, the

Wellamo [Wolayta] Nation, the Adere [Harari] Nation, and however much you may not like it the Somali Nation."

የነ "ፋኖን" መጽሐፍ በማንበብ በስሜት የተወነጨፈው ወጣቱ ዋለልኝ "አገር ማለት አንድ የቋንቋ ልሳን፤ አመጋገብ፤አለባበስ፤ አንድ የተሳሰረ ማሕበራዊ፤ምጣኔ ሀብታዊ፤ እና ተመሳሳይ የጋራ ታሪክና ድምበር፤ ሲኖረው ብቻ ነው አገር/ብሔር ወይንም አንድ ሕዝብ ሊባል የሚቻለው፡ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ የብሔሮች ስብስብ እንጂ፤ ይህንን ያላሟላች ባሁኑ ጊዜ እራስዋ የቻለች አንድ ወጥ የሆነች አገር አይደለችም"። ይላል። ብሔር በትክክለኛ ትርጉሙ "አገር ማለት ነው"። ዋለልኝ የሚለን ደግሞ ኢትዮጵያ የተለያዩ አገሮች ያቀፈች ብሔር/አገር ነች ይለናል። አገሮች የሚላቸው ደግሞ ሲተነትን ኦሮሞ ነሺን/ ብሔር/አገር አማራ ነሺን/አገር/ብሔር ሲዳማ ጉራጌ ነሽን/ አገር ወዘተ...ወዘተ. የተባሉ አገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ይላል።

የፋኖን መጽሐፍ አንባቢው ዋለልኝ ሊቃጣው የፈለገው "ኢትዮጵያ የተጠቀሱትን አገሮች/ብሔሮች ኮሎኒያሊስት ነች" ለማለት ነው። እንደ አገር ሳይሆን አንደ ጭቃ ተጠፍጥፋ አማራዎች እና ትግሬዎች ያገጣጠሟት አሁንም የሚገዝዋት "የውሸት ስራ የሆነች አገር በመባል የምትጠራ "ፌክ ኢትዮጵያ" የምትባል በአማራ ገዢዎች የሚቀሰቀስ ኢትየጵያዊ ስሜት እንጂ በውስጧ የሚኖሩ ኗሪዎቻ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት የሌላቸው የውሸት አገር ነች" ሲል ይወነጅላል። ዓድዋ፤ ማይጨውና የመሳሰሉ ኢትዮጵያዊነት ስሜትን ለዓለም ያስመሰከረ ሕዝብ "በውሸት ስሜት" የሚነዳ ሲል

ሕዝብን ይዘልፋል። ስለ አገሪቱ ብሔራዊ ስሜት የመሰከሩ የውጭ የታሪክ ሰዎችም አብሮ ይገርፋቸዋል።

PREVAIL – THE WAR IN AFRICA THAT CHANGED THE WORLD [Book Trailer]
https://youtu.be/iN3wCyfDbwY

በምንሊክም፤ በሃይለስላሴም ዘመን ጠላት አገሪቷን ለመውረር ሲመጣ፤ ኦሮሞ፤ አማራ፤ትግሬ፤ጉራጌ፤እስላም ክርስትያን ሰይል ባብዛኛው ፤በብሔራዊ (ሃጋራዊ) ስሜት ተነስቶ ጠላት ድል በመምታት፤ ሊደርስ የነበረው ውርደት ቀንሶ አንዳንዴም ጭራሽኑ ዓለም በሚያስገርም ጀብዱ ተዋግቶ ጠላትን አሳፍሮ መልሶዋቸዋል። እነኚህ ልባቸው፤ቀ፤ቀባቸው፤ ሕሊናቸው አካላቶቻቸው ሁሉ ባገር ፍቅር፤በብሔራዊ ስሜት የተገነባ ነው።



ያውም በተደጋጋሚ! እነ ዋልልኘ “ፌክ’ኢትዮጵያ፤ “ስሜተ ቢስ ዜጎች፤ እያለ ያዋረደው ሕዝብና አገር።ዋልልኘ ያ ሁሉ ጀግንነትና ጀብዱ፤የገዢ መደቦች ብሔራዊ ስሜት ያነሳሳው፤የገነባው እንጂ ሐቀኛ ሃገራዊ ስሜት የተንጸባረቀባት አገር አይደለችም፡ ይላል። ከላይ የሰጠኋችሁ የመጽሐፍ/ቪዲዮ ማስታወቂያ፤ ጣሊያን ሲወጋን፤ ብሔራዊ ስሜታችንን ለመግደል ሲዘምትብን፤ እንኳን ኢትዮጵያዊያን ቀርቶ፤ የውጭ ዜጎችም (ዋለልኘ ተጓዦች/ጎብኚዎች ይላቸዋል ሲያሳንሳቸው) ብሔራዊ ስሜታቸው ከኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ ስለነጎደ ፤ስሜታቸው ተጋግሎ በመላው ዓለም ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ በቪዲዮው እዩት። የዋለልኘ ስሕተት በግልጽ ይታያችኋል።

አገራዊ ስሜት ሽማግሌዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ወራሪ ሲመጣ ወጣቱም በእንዲህ ያለ አገራዊ ስሜት ተገንብቶ ነበር ጠላትን ያርበደበደው፤



ከእነዚህ ከላይ በፎቶግራፍ ከተመለከትናቸው የአገር አርበኞች የተላላፈ ብሔራዊ ስሜት፤ የትግራይ ፋሺስት ግልገሎቹ ከትግራይ ገስግሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የወደብ ጉዳይ እና የኤርትራ ግንጣላ የሴራና የባንዳዎች ውሳኔ ነው ብለው የግራዘያኒ ጥይት እሩምታ ሲያወርዱባቸው፤ የኢትዮጵያ ፈጣሪ ይመስገን "ኢትያዊ ብሔራዊ ስሜት" አልጠፋም ነበር። ይህንን ታሪካዊ እና rare/ የማይገኝ እግዚሄር እራሱ ያነሳው ታአምራታዊ የአምላክ ስራ/ፎቶን" አብርን እንመልከት። አሌፍ በተባለው መጽሔት ታትሞ ነበር። እነሆ፤




ዋለልኝ፤ “There is of course the fake Ethiopian Nationalism advanced by the ruling class and unwillingly accepted and even propagated by innocent fellow travellers. ይላል።

ዋለልኝ በህይወቱ እያለ የሕዝቡ ኢትዮጵያዊ ስሜት እንዴት ግሎ እንደነበርና “በአገርና በሚስት የለም ዋዛ” ብሎ መመሪያው ያደረገ “አንድ” ሕዝብ፤ እንዴት እንዳልገባው ባይገባኝም፤ በሃገራችን የታዩ ተደጋጋሚ ጀብዶች (ከጦርነት እስከ ስፖርት) የገዢ መደቦች የፈጠሩት ከሆነ፤ ከሕዝቡ ይልቅ ለገዢዎች ግርማ ሞገስ መስጠቱ የዋለልኝ ግምገማ ለእኔ አስገርሞኛል።

ገዢዎች መመስገን የሚገባቸው ቦታና ክብር ፣መስጠት ያለ ነው፤ ምክንያቱም ሃገራዊ ስሜቶች መሪዎች ናቸው የሚመሩት፤ከዚያም ሕዝቡ ሆ ብሎ ይከተላል።ሆኖም የተገኙት ድሎች ያለ ብሔራዊ ስሜት የተገኘ ነው ብሎ የሚያምን ምሁር ሁሉ "ያስተሳሰብ ችግር አለበት ማለት ነው። የዓለምን ኢምፔሪያሊሰት ወራሪ ፋሺስት ዓድዋ ተራሮች ላይ "ማማ ሚያ!!!!እማዬ ሆይ! እማዬ ድረሺ!" እስኪል፤ በእምብርክኩ ያስኬደው ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት የት ሊደበቅ ነው? የሕዝቡ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ያመነጨው ድል ካልሆነ ምን ተብሎ ሊጣራ ነው?

የመጠቁ የተመነደጉ ተማሪዎችና አንዳንድ የወቅቱና የዛሬ ምሁራን አማራ ስለሚጠሉ፤ አማራን በገዢ መደብ ስለሚመድቧቸው፤ መሪዎችን እየዘለፉና ያሳነሱ እየመሰላቸው የሕዝቡን የጀብዱ ተሳትፎ፤ ከሕዝቡ ነጥቀው "የአማራ ነው" የገዢ መደብ ነው" እያሉ እራሳቸውን ያስገምታሉ። ጥላቻ እስከዚህ ድረስ የሕሊናን ሚዛን ይጋርዳል።

የላይኛው ክርክሬን ለማጠቃለል፤ ዋለልኝ የሚለን፤ ኢትዮጵያ አንድ አገር አንድትባል፤ አንድ ቋንቋ፤ባሕል፤አለባበስ፤አመጋገብ፤ስነሉቦና፤ ባሕል ሲኖራቸው አንጂ የተለያዩ ቋንቋዎች፤አለባበሶች፤ባሕሎች፤ አመጋገቦች ያሉባት አገር "አንድ አገር/one nation" ልትባል አትችልም። ሲል በመላ ዓለም one nation/ አንድ አገር/ አንድ ሕዝብ ተብለው እንደ አገር የሚጠሩ አገሮች በሙሉ በውስጣቸው የተለያዩ ቋንቋዎች፤ባሕሎች፤አመጋገቦች እና አስተሳሰቦች ያላቸው መሆናቸውን ለምን አንዳልተረዳው ለኔ በጣም ግራ ይገባኛል።

ሰው ተብሎ የሚጠራ ሁለት ፆታ ይዟል *ሴት* እና ^ወንድ*። ነገር ግን ሲጠሩ በጥቅል/በጋራ መጠሪያቸው ሰው ተብለው ነው የሚጠሩት።አገርም የተለያዩ ጎሳዎች ፤ቋንቋ፤ቀለም፤ቁመና፤አለባበስ፤ ባሕል....ይኑራቸው እንጂ በአንድ አገር የሚኖሩ፤ የአንድ አገር ሕዝብ ናቸው።

የተለያዩ ዛፎች ሲሰበሰቡ፤ ምን ተብለው ይጠራሉ? *ጫካ"። የኢትዮጵያ ሕዝብም 'ትግሬ፤አማራ፤ጉራጌ፤ሶማሊ ጋምቤላ ኦሮሞ...." ይባሉ እንጂ እንደ ተሰበሰበው እያንዳንዱ ዛፍ 'ጫካ' ተብሎ አንደሚጠራ ሁሉ የተለያዩ የእነዚህ ነገዶች ስብስብም በጥቅል "የኢትዮጵያ ሕዝብ" ይባላል። ምክንያቱም ፡ግለሰብ" ሲሰበሰብ "ሕዝብ" ስለሚሆን። ሆኖም፤ የሚታየው ሕዝብ ሳይሆን ፤ሰው ነው፤ ግለሰብ። ሕዝብ ቁጥር እንጂ ምንም ማለት አይደለም። ሰው ፤ግለሰብ ግን የሚዳሰስ የሚጨበጥ "እውነታ" ነው።

የማርክሲስቶች "ብሔር፤ብሔረሰብ" የሚባል "የግሩፕ" መብት "ለስልጣን መወጣጫ፤ለግንጣላ" የተሴረ እንጂ "ብሔር/ብሄረሰብ" የሚባል መብት የለም። ሰው፤ሰው በመሆኑ ብቻ እንጂ "ነገድ/ሕዝብ/ክምችት/በቡድን" ስለሚጠራ አይደለም መብቱ የሚከበረው። ስለ እኩልነት እና መብት ስንነጋገር "የግለሰብ" መብት ብቻ ነው ያለው። ያለ ግለሰብ ምንም ነገር የለም። ዛፍ እንጂ እውነታው፤ ጫካው አይደለም። የሚታየው ዛፍ እንጂ ጫካ የዛፍ ስብስብ ነው። ዋለልኝ የሚለን፤ የብሔር/ብሔረሰብ መብት (የግሩፕ መብት ነው) እንጂ የግለሰብ መብት አይደለም የተከራከረው። እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ብሔር ነው መብትህ መከበር ያለበት ይላል። ይህ ደግሞ "ብዙሃን

ለጥቂቶች ይገዙ ነው"። ዲካቶሪያል ዲሞክራሲ የሚባለው ማለት ነው።

በሌላ መልኩ የዋለልኝ "ዲሞክራሲ" ሰው/ለግለሰብ/ መብት እየጣሰ
'ግሩፕ/ብሔር/ብሔረሰብ' ለሚባል ጨቋኝ "ቡድን" ነው የሚሰጠው። ይህ ደግሞ "ዲሞክራሲ/ፋሺዝም/ማርክሲዝም/... ርዕዮት እንጂ "ብዙሃን በጥቂቶች" ወይንም "ጥቂቶች በብዙሃን" የመብት መረገጥ የሚጻረረው "ሪፓብሊካዊ" ርዕዮት አይደለም መስፈን ነበረበት ብሎ የተሟገተው "ዲክታቶሪያል ሞክራሲ" ነው እየሰበከ የነበረው። የአሁኑ ወያኔዎችም ሆኑ አነጎች "ይህንኑ ብዙሃን/የቡድን" መብት ነው እያካሂዱ ያሉት። ኮሆርዥን (ማስገደድ) ነው መበት የሚሉት። ጥቂቱ ወይንም ብዙሃን ይመውኡ/ዲሞክራሲ፤ እያሉ ግለሰብ እንዲረገጥ ይፈቅዳሉ፤ በሕግ ይደነግጋሉ። ዲሞክራሲ በመሰረቱ "እኩልንትን የሚያስከብር ስልት አይደለም። በብዙ መልኩ የብዙሃን መብት አስከባሪ ሆኖ የጥቂቶች ረጋጭ ሆኖ የሚከተልበት ወቅት አለ።

የአማራን የግለሰብ መብት መረገጥ በኦሮሞ፤በሶማሌ እና በሲዳማ/ወላይታ...በመሳሰሉ አካባቢዎች "ብዙሃኖቹ ኗሪዎች የጥቂቶችን የአካባቢ ነዋሪዎች የመርገጥ መብት ስለ ተፈቀደ ነው"። የቡድን መብት ውጤት የግለሰብን ወይንም የጥቂቶችን መብት በመርገጥ መብት (እኩልነትን) ይጻረራል። ዲሞክራሲ እራሱ በጥልቅ ስንመለከተው "ኮሆርዥን ነው/አስገዳጅ" መብት ነው።የነ ዋለልኝ ብሔር ብሔረሰብ የራስ ገዝ/አስተዳዳር እስከ....ወዘተ

የሚሉት ይህንን የግለሰብ የመብት ረገጣ ስልት እውን ለማድረግ ነው።

ዋለልኝ፤ አላዋቂ እንዳይባል፤ ከሊቅነትም በጣም ሊቅ እና ብልሕ ነው። ነገር ግን ለዚህ ድንቁርና ድምዳሜ ሊያደርሰው የቻለው “ምን አንደሆነ የታሪክ/የስነ ሉቦና/ ኣኢምሮ ሊቃውንት ሊፈትሹት ይገባል።

የላይኛውን አስተሳሰቡ ግልጽ ሲያደርገው ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

“This is the true picture of Ethiopia. There is of course the fake Ethiopian Nationalism advanced by the ruling class and unwillingly accepted and even propagated by innocent fellow travelers. What is this fake Nationalism? Is it not simply Amhara and to a certain extent Amhara-Tigre supremacy? Ask anybody what Ethiopian culture is? Ask anybody what Ethiopian language is? Ask anybody what Ethiopian music is? Ask anybody what the "national dress" is? It is either Amhara or Amhara-Tigre!! To be a "genuine Ethiopian" one has to speak Amharic, to listen to Amharic music, to accept the Amhara-Tigre religion,

Orthodox Christianity and to wear the Amhara-Tigre Shamma in international conferences. In some cases to be an "Ethiopian", you will even have to change your name. In short to be an Ethiopian, you will have to wear an Amhara mask (to use Fanon's expression). Start asserting your national identity and you are automatically a tribalist, that is if you are not blessed to be born an Amhara. According to the constitution you will need Amharic to go to school, to get a job, to read books (however few) and even to listen to the news on Radio "Ethiopia"
unless you are a Somali or an Eritrean in Asmara for obvious reasons."

አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ "አማራ" ካልሆነ በቀር ወይንም "የአማርኛ ስም ከሌለው" የስራ ዕደል "አያገኝም" መሰረት እና በማስረጃ የማይደገፍ ጽሑፍ በትኗል። ስራ ለማግኘት አማራን መምሰል አማርኛን መናገር ያስፈልጋል ይላል። ትንታኔውን ከላይ በጥንቃቄ አንብቡት።

አንባቢዎቹ ሆይ፤ የመንግስት ስራ ለመቀጠርም ሆነ ፤ ሕዝባዊ ተቋማትን በሚያገለግሉ የግል ተቋማትም ሆነ ተዘዋውሮ ንግድ ለመነገድ ብሔራዊ የመገናኛ ቋንቋ ከሌለ በምን ይግባባል? አይደለም እንዴ? የጋራ መገናኛ ሆኖ በታሪክ አጋጣሚ በሁሉም ቦታዎች የተንሰራፋው ደግሞ "አማርኛ" ነው። ታዲያ አንድ ኢትዮጵያዊ "አማርኛ" ካልቻለና ካልተማረ፤ በምን ቋንቋ ተግባብቶ ንግድም ሆነ በመንግስት አገልግሎት ተቀጥሮ ባገሪቱ ቦታዎች ተዘዋውሮ ሊያገለግልና ከሕዝቡ ጋር ሊግባባ ይፈለጋል? አሁን እየታዬ ያለው የወያኔ የትምህርት/በደምብ ያልተጠና የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል ውጤት እያየን ነው።

"በ69 በሶማሌ ወረራ ጦርነት ጊዜ ወደ 300 ሰልጣኝ ሰራዊት ታጠቅ ጦር ሰፈር ለስልጠና የገባው አንዳንዱ ሰልጣኝ፤ አንድ ወጥ የሆነ የመገናኛ ቋንቋ የነበረንን "አማርኛ" መረዳት ስለማያውቅ፤ ለወታደራዊ ስልጠና "ግራ ቀኝ" የሚለውን "ሀ" ብሎ ሰልፍ ሲማር "ቃርያና ድንች በግራና በቀኝ እጁ እንድይዝ ተደርጎ ነው "ቃርያ፤ ድንች" ፤ "ቃርያ ድንች" እያሉ ጀምረው በሦስት ወር ወታደራዊ ስልጠናው አጠናቅቆ መሰረታዊ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ተምሮ "ሰራዊቱ" አንድ ሆኖ ትዕዛዝ ማክበርና በማድመጥ ባስደናቂ ሁኔታ በጠላት ላይ የዘመተው" ይላሉ አቶ ተክሌ የሻው።

። በታሪክ አጋጣሚና በገበያ ዕድል የገጠመው አንድ ቋንቋ የሕዝብ መነጋገሪያ ሆኖ መገኘት በኢትዮጵያ የተደረገ አይደለም። መላው ኣለም በዚህ ስልት ነው የሄደው። ሁሉም ቋንቋ መነጋገሪያ ማድረግ አይቻልም። ዓለምም አላደረገው ኢትዮጵያም ላድርግ ብትል አትችለውም። ይላሉ የሞረሽ ፕረዚዳንት አቶ ተክሌ የሻው።

አቶ ተክሌ አያይዘውም እንዲህ ይላሉ፡-

“አማርኛ በታሪክ አጋጣሚ የወታደር መነጋገርያ ሆኖ ሲፈጠር በመላ አገሪቱ ወታደሩ ሲዘምት እየተግባባ ያመረተው አማርኛ ገበያተኛ አገኘ። የመገበያያም ሆነ የመንግሥት ሥራ መግባቢያ አማርኛ ይሁን እንጂ፤ ከላይ ስርአቱን የመሩ መሪዎቹም ቢሆኑ ከጉራጌ፤ ከአፋር፤ከትግሬ፤ ከወላይታ፤ ከአማራ፤ ጉራጌ የተገኙ ናቸው።

በአጼ ምኒሊክም ሆነ በሃይለስላሴ ዘመን መረጃውን ልጀምርልህ፤ ይላሉ አቶ ተክሌ፡-

ተማሪው አመርኛ ቋንቋ የመገናኛ ቋንቋ በመሆኑ ብቻ አማራ በላይነት ተቀዳጅቷል፤ በማለት አማራን ወንጅለውታል። የተሳሳተ ነው! አማርኛ ሕዝብን እያግባባ ጠቀመ እንጂ አልጎዳውም። ባይሆንማ በምኑ ይግባባ ነበር? እስቲ አሰቡት? አማራው ደረቱን ለጦር፤ እግሩን ለጠጠር አድርጎ ለኢትዮጵያ አንድነት ሲሞት፤ ሲገብር ነው የኖረው። የረባ አንድም ነገር ለራሱ አላደረገም። ሲንከራተት ነበር የኖሮው፡ ለዚህ ነው አገር ሲያቀና አይተውት “ነፍጠኛ የሚሉት”። ማቅ ለብሶ እኮ ነው የመንዝ ሰው የሚኖረው ዛሬ! የመርሃ ቤቴ ሰው እኮ የአመት ቀለብ፤ የአመት ልብስ የለውም እኮ! ጫማ እኮ የለውም፤ ብረድልብስ እኮ የለውም። ወያኔዎች እንኳ  አማራ በሚኖርበት አካባቢ ሲያልፉ “ትግሬው በኑሮው ይሻላል፤ ይህንን አይተናል” ብለው እራሳቸው መስክረዋል (ስብሓት ይህንን በቃሉ መስክሯል፡ አውድዮው አለን።) አማራ ከሌላው የተሻለ ነው የሚሉት ስልጣን ለመቆናጠጥ ሲመኙ ነው። መለስ ዜናዎ የትግራይን ሕዝብ ያሞኘው “አማራ እንዲህ አደረገህ” እያለ ትግሬ እንዲከተለው ያደረገበት ስልት ይህንን የዋለልኝን ትምህርት በመከተል ነው።

ያንን የሚሉ ሰዎች የአማራውን ኑሮውን ወደ ኋላ እመለስበታለሁ። የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ሲሉ አገሪቱን ለረዢም ጊዜ ያስተባበረና አንድነቷን የገነባው “አማራን፤ ዘውድን፤ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን/ተከታዮቿን” ማፍረስ ነው ብለው ተነሱ። ይህንን ቅስቀሳ የውጭ ጠላቶች ይህንን ለወያኔ እና ለሻዕቢያ አስተላለፉለት። ተማሪው ሳይገባው **“እያ በሬ ሆይ ሳሩን እያየህ ገደሉን ሳታይ....”** በሚል የኢትዮጵያ ታመሪዎች የዚያ ቅስቀሳ ሙርኮኞች ሆኑ። ዘውዱን አፈረሱት። ቤተክርስትያኒቱ ሃይልና ስልጠን አጣች፤ተከታዮቿ እና መሪዎቿ ተበተኑ። ማን ቀረ? አማራ የሚባል! ይህንን የቀረው ደግሞ መለስ ዜናዊ የትግሬን ሚሊሺያ ተዋጊ ይዞ ገባ እና ሕዝቡን አሳስቶ “አማራውን ከተከተው”።

ቀደም ሲል በመደብ ትግል፤ በኋላ ጸረ ፍጠኛ ትግል፤ከዚያ የብሔር ብሐየረሰብ ጨቛኝ ትግል.... እያሉ ጨፈጨፉት። የዋልልኝ ተከታዮች እነ ወያኔዎች እኮ “አክሱም ለጉራጌው፤ለሃዲያው፤ ለአማራው ምኑም አይደለም” ብለው ተናገረዋል; የወያኔው የእስር ቤቶችና የስለላ አቀናባሪ የነበረው ብስራት አማረም ያንኑ ደግሞ “ፍኖተ ገድል” የሚል መጽሐፍ ጽፏል።

ስልጣንከን ‘አማራ’ ስለያዘው ነው፤ የሸዋ አማራ ስለያዘው ነው” ሲሉ ዋሽተዋል። ንጉሦሱ እንውሰዳቸው፡- በንጉሡ ጊዜ ማን ነበር ሥርዓቱን የመራው? አማራው በብቸኝነት ሥልጣን ይዞ አያውቅም።
የሸዋ አማራ የሚባል አባባል አላቸው ተማሪዎቹ፡ ማንን ነው? የሸዋ አማራ የሚሉትን እንመለከት እስቲ? ቀ/ሃይለስላሴ አማራ፤ ጉራጌ ኦሮሞ ናቸው/ትግሬም እንወለዳለን ብለዋል። ቀ/ሃይለስላሴ መኮንን፤ መኮንን ጉዲሳ ናቸው። እናታቸው የሺ እመቤት፤ የሺ እመቤት ጋንዶሎ ጉራጌ ናቸው። ከሃያ በላይ ኤርትራኖችና

ትግሬዎች በንጉሡ ዘመን ከፍተኛ ሥልጣን ነበራቸው፤ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ ጌታቸው ረዳ ባለፈው አመት ባንድ ጹሑፉ ላይ በጥቅስ ያስቀመጠው በንጉሱ ዘመን ኤርትራኖችና ትግሬዎች የሆኑ የባለስልጣኖች ስም ዝርዝር ይመልከቱ)። እንዴት ነው ነገሩ! ስለ ሃቅ በሃቅ እንነጋገር እንጂ!

የምንሊክ መንግሥትስ? ዓለም የሚያውቃቸው ዓለም አቀፍ ቄሳርን ያምበረከኩ አፄ ምኒሊክ፤አማራ ብቻ አይደሉም። እናታቸው እጅጋየሁ አድያቦ ጉራጌ ናቸው። በየት መጥቶ ነው አማራ ነገሰ የተባለው? የጦሩ ገበሬው እኮ ገበየሁ እኮ ኦሮሞ ነው፤ ባልቻ አባ ሻፎ እኮ ኦሮሞ ናቸው፤ ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) እኮ ኦሮሞ (?) ናቸው። እነዚህን አስተባብረው ድልን 'ስልጣንን የገነቡ ዓለም ያደነቃቸው ቅይጥ ነገዶች ናቸው። ዝርዝር ውስጥ ብንገባ አማራ የሚባል ስልጣኑን ያልተጋራ መሪ አልነበረም። መዋሸት ይብቃ። ሃቁን እናፈርጠው!

*አሁን ደግሞ ወደ ደርግ ጊዜ ልውሰድህ*

"እግረኛ ወታደሩን ተመልከተው። የትኛው ነው አማራ ብቻ የሆነው ወታደር? ስለጣን ላይ ያሉትንስ? መንግስቱ ሃይለማርያምን ብትመለከት አማራ፤ኦሮሞ ናቸው።እነ ደበላ ዲንሳ ምንድናቸው? እነ ተካ ቱሉ ምንድናቸው? እነ ተስፋዬ ገብረኪዳን ኦሮሞ እኮ ነው፤ ተስፋዬ ገብረኪዳን ስለተባለ ትግሬ ይመስለዋል ሰው። ዉብሸት ደሴ ኦሮሞ እኮ ነው፤ አየር ሃይሉን የተቆጣጠሩት እነ መርዕድ ንጉሴን እነ ጀኔራል ረጋሳ ጅማ እኮ ኦሮሞዎች ናቸው፤ ስንቱን ልቁጠርልህ፡ 'ኦሮሞዎች" ናቸው። ስለዚህ አማራ ስልጣኑ ተቆጣጥሯል፤ ወይንም አማራ አደገ ብትለኝ፤ እነ ቡልጋ፤ሸንኮራ፤እነ ፋርጣ፤ጭልጋ፤ አጣቃላይ ጎጃምን ውሰደው፤ ወሎ፤ የተሻለ ት/ቤት፤

ጤና፤ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ አደገ ፤አድልዎ ተደርጎ አማራው አድጎ ነበር እንል ነበር፤ ያ ግን አልሆነም።ከየት መጥቶ?” ሲሉ የሞረሹ አቶ ተክሌ የሻው መረጃቸውን አቅርበው በሚገባ በእርግጠኛነት በኩራት ይከራከራሉ።

ዋለልኝ አማራ ሆኖ መወለድ ዕድለኛ መሆን ነው ይላል። ይህ አባባሉ ግን ፍጹም የተጋነነ ነው። አማራው አይደለም ወይ በወሎ ድርቅ የተገረፈው? የጎጃም አማራ አልነበረም ወይ በንጉሱ ቦምብ የተደበደበው? “ጥሩ ኢትዮጵያዊ ለመባል የአማርኛ ሙዚቃ ማድመጥ አለብህ” ይላል ዋለልኝ። ምን እሚሉት ደንቁርና ተጠናውቶት ነበር ዋለልኝ እንዲህ ሊል የቻለው? ሙዚቃ እኮ ወገን ፤ጎሳ፤ዘር አይለይም። ዓለም አቀፍ ነው። እንኳን ሰውን ‘ሙዚቃ’ የአራዊትን ስሜት ሳይቀር ይቀሰቅሳል።

የአማራ ሙዚቃ ደግሞ ካፈጣጠሩ በሽተኛን ከአልጋ ቁራኛነቱ የሚያስነሳ፤ ምናልባትም የሞተንም ሰው የሚቀሰቅስ፤ ጣእም ያለው፤ሽማግሌንም ሳይቀር የሚያስጨፍር፤ የሚያስተክዝ፤ አንሰቅስቆ የሚያስለቅስና ከተቀመጥክበት ወደ ማዶ አሻግሮ ልብሕን ሰርቆ እንደ ወፍ ወደ አገርህ ወደ ፍቅረኛ የሚያከንፍ፤ ሴትም ወንድም ማራኪ፤ በአንዳች ነገር የተቀመመ፤ አደንዛዥ የሆነ የፈጣሪ ስራ መሆኑን እንዴት ዋለልኝ የወላጆቹን ሙዚቃ ምንነት ሳይረደው እንደቀረ ሳስበው ለኔ ለጌታቸው ረዳ ግራ ገብቶኛል።

የአማራዎች ሙዚቃ እንኳን ዜጎች ቀርቶ ዛሬም እንኳ ኤርትራኖች አማራን በሃሰት ተበክለው ባወገዙበትና በጠሉበት ወቅት ከአማርኛና ሙዚቃ ሌላ ሙዚቃ አያዳምጡም። አማርኛ ቋንቋና እና አማራና አማርኛን ኩፉኛ የሚጠላ ኢሳያስ አፈወርቅ አንኳ ጥላሁን ገሰሰ ሲሞት ለጥላሁን ሙዚቃ ያለው አክብሮት

የተናገረው ምን እንደሆነ ምስክር ነን። ጥላሁን ደግሞ የታወቀባቸው ሙዚቃዎቹ አብዛኛዎቹ "አማርኛ ናቸው"። አማርኛ ሙዚቃ ሕዝቡ ሲያደምጥ የነበረው አማራ ለመምሰል ሳይሆን ፤ በስልቶቹ ቃና እና እስክስታ አመታቱ ስለተማረከ ብቻ ነው። እውነታው ይኼ ነው።

ዛሬ ወያኔ ያንኑ የዋለልኝ "አማርኛ ይጥፋ፤ አማርኛ ጨቋኝ ነው፤ ኢትዮጵያ የምትባል "ፌክ" አገር ነች" ወዘተ ..ወዘተ.ወዘተ ,፣ ስብከቱን የተከተሉት የዛሬዎቹ ወያኔዎች፤ አገሪቱ "ባቢሎን" አድርገዋት ዜጎች እርስ በርሳቸው እንዳይግባቡ አድርጎ ፤ ባዕድ ሆኖ እንዲተያይ እርስ በርስ ሲባላ እያየን ነው። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ዋለልኝ ሕዳር 10/1961 "ታገል በሚባለው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መጽሔት ላይ 'የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ' (On the Question of Nationality in Ethiopia) ያሰተመው ጽሑፉ ለዛሬ ባቢሎናዊ ምስቅልቅል የወያኔ ግራ ዘመም ፋሺስታዊ አስተዳደር አስተዋጽኦ ከፍተኛ ድርሻ አለበት የሚል አምነት አለኝ።

ስለሆነም ነው ወያኔዎችም ሆኑ ኦነጎች እና ኦጋዴኖች "ዋለልኝን እንደ አርበኛቸው የሚመለከቱት"። በአማራው ላይ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የአገሪቱ የውስጥም የውጭም ጠላቶች አማረውን ጥርሳቸው ውስጥ በማስገባት ጊዜ ጠብቀው ብትር በመሰንዘር "ነፍጠኛ" የሚል ቅጽል ስም በመስጠት ከደቡብ ከምስራቅ፤ ከምዕራብ፤ እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ እየተገደለ፤ ከኑሮው እየተፈናቀለና እየተባረረ ወደ አገርህ ሂድ ለመባል የበቃው።

በሕይወት የሌለው ዋለልኝ ስለ አማራው እንዲህ አጣምሞ ተማሪውን ሲቀሰቅስ፤ በሕይወት የሚገኙት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሶማሌ "ክልል" ውስጥ አማራዎች እንጂ ትግሬዎች ጠላታችን አይደሉም እያሉ የክልሉ አስተዳዳሪዎች በግልጽ ለመናገር

የበቁት ፕሮፌሰሩ አስተዋጽኦ የለበትም ማለት ይቻላል? ይህነን እስኪ በዩ ቱብ ስዕለ ድምፁን በዓይናችሁ እና በጆሮአችሁ እነሆ አድምጡ።

TPLF puppet Somali president secret video exposed TPLFs hate against Amhara May 8 2013 https://youtu.be/Kj2sNJ5B2j0

በሚቀጥለው ሰሞን ደግሞ ስለ ልዑል ራስ ስዩም መንገሻ ወይንም ስለ ጋዜጠኛዋ ወደ ብዙ ወንድማገኘሁ በሚቀጥለው ሳምንት እንመለከታለን።

አመሰግናለሁ፤

ጌታቸው ረዳ

(Editor Ethiopian Semay) getachre@aol.com

# Where is Tsegaye Debtraw ?

## By Getachew Reda,
## San Jose, California

Whenever I was late at night & my mother have no clue where I am, while I am having a good time with my friends outside, my mother use to say "have you heard crying or seen the Hyena who eat my son Getachew?" jokingly some times seriously.

When it comes to Tsegaye Debteraw & his friends who were kidnapped (may be killed afterwards ) from the forest with the order of TPLF officials; it is not a joking matter if we say have you heard crying or seen the Hyena who eat Tsegaye Debteraw? I am sure their mothers are not only saying the way my mother use to say, but also demanding to know the killer or the kidnappers of their beloved sons.

I am sure most of you have heard as I do, that the former Dictator Mengistu Haylemariam's latest interview which is published by the TPLF Mega Publishing and Printing Center. Mengistu in his interview, he strongly asserted, he have no hands what so ever or no clue who killed the popular author Bealu Girma, the author of the popular book OROMAY.

Would it be decent if we ask the so called dissenters who were the

X-officials of the TPLF such as Gebru Asrat, Alemseged GebreAmlak, Tewolde and the rest of the members of the decedents group WHERE IS TSEGAYE DEBTERAW? Would it appropriate also if we seek an answer from the two former officials namely Ato Gebru Asrat and Ato Alemseged GebreAmlak Who are already here with us in the Diaspora, if they can explain to the public voluntarily, so it helps the victims family and friends know to what happen and where about is Tsegay Debteraw with his kidnapped friends.

Whom these officials I am positive have a full knowledge of information regarding to what happen to these political victims after they kidnapped them? Can they tell us if they know why the Hyena who eat Tsegaye and his friends is not crying? Can Finote Radio or any one in the business of report and journalism get contact those former officials and interview them, so that the public, most of all their family can be informed what happen to their sons and brothers/sister?Can we ask if Ato Alemseged GebreAmlak be decent and kind most of all be concerned Ethiopian, if he can kindly inform or discuss this issues and the likes to the public as well in 'addition" to his subject of lecture" of how they split from their organization? I am sure Gebru Asrat or Alemseged are free to discuss or reveal any sensitive information to the public with out pressure or fear from any body, since they live and move freely in the Diaspora where their state of mind is ready to discuss all issues with the public (If my guess is not wrong). Most of all, they have to insist themselves to be the first officials to expose such hidden secrets and other highly sensitive issues. Most of all, kidnapping and killing culture of TPLF must be exposed by and ridiculed by these officials in-front of the public for the decency and future clarity if they are ready to confess.

I bring this issue as a decent Ethiopian who cares about every life lost by TPLF. Dr.Taye Is free because we cry loud to the world, why not we cry for Those who perished with out seeing any court of justice? Aren't they too leaders of student movements and leaders of political organization who spoke on behalf of their people? If we start demanding to know where about the sons and Daughters of the Ethiopian mothers & fathers who were kidnapped by TPLF and EPDM who are still perished with no clue where their about is : then that means we are preparing our mind to teach not to accept indecency and lies .

Most of all we know to what is happening to those who are in the custody of TPLF, who are officially seeing the TPLF , Courts in our cities and towns,. But what is not clear and where about their presence is, THE PEOPLE WHO ARE KIDNAPPED FROM SUDAN LIKE MY FRIEND LEUTENANT DESTA WOLDEMIKAEL (ADUWA>ADI-ABUN THE BROTHER OF MEMHIR ABRAHA WOLDEMIKAEL) AND OTHER VICTIMES

VIOLENT ORGANIZATION. This is where we have to start demanding the officials to expose hidden secrets with all the story and responsibility they know.